# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 141 ጥር 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የኢትዮጵያ ፕሬስ ጽርጅት

## - የራሱ ማተሚያ ቤት አለመኖሩ ቁልፍ ችግር ሆኖበታል
## - በ6 ወራት አፈጻጸም ከእቅዱ 91 በመቶ በላይ አሳክቷል

መማር ደበልጣል

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የራሱ ማተሚያ ቤት አለመኖሩ ቁልፍ ችግር እንደሆነበት ተገለፀ።

የኢፕድ ባለፉት ስድስት ወራት ተጨባጭ ለውጦችን ማስመዝገቡን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን የስድስት ወራት አፈፃፀም ገምግሟል፡፡

የግማሽ ዓመቱን አፈፃፀም ያቀረቡት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሔለን እስክንድር እንደገለፁት፤ በግማሽ ዓመቱ 145 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ155 ሚሊየን በላይ ገቢ ተሰብስቧል።

የገቢ አፈጻጸሙም ከእቅዱ አንፃር 107 በመቶ ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- በላሙኤል ተስፋዬ



አቶ ጌትነት ታደሰ — አቶ እውነቱ አለነ









# የኢንዱስትሪ ዘርፉ በአስር ዓመቱ መሪ እቅድ፤

## - የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ያደርሳል
## - ለአምስት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል
## - የተኪ ምርት መጠንን 60 ከመቶ ለማድረስ እየሠራ ነው

ወርቁ ማሩ

ጎንደር፡- በአስር ዓመቱ ስትራቴጂክ ዘመን የኢንዱስትሪ ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ እየሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ሚኒስቴሩ ለአምስት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር እና የተኪ ምርት መጠኑንም አሁን ካለበት 30 በመቶ ወደ 60 በመቶ ለማድረስ እየሠራ መሆኑን አስታውቋል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ለኢትዮጵያ

የኢንዱስትሪ ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ

# በአስር ዓመታት ለ20 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ ፡- በአስር ዓመታት ለ20 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ታቅዶ በመሠራት ላይ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ ፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የስድስት ወር ሥራ አፈጻጸሙን ከክልሎችና ከተጠሪ ተቋማት ጋር ከጥር 17 እስከ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ገምግሞ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን አስቀምጧል።

ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ



የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን በግምገማው ማጠቃለያ ላይ እንደገለጹት ፤ ተቋሙ በአስር ዓመት ለ20 ሚሊዮን ዜጎች ሥራ ዕድል ለመፍጠር

በአስር ዓመታት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ክልሉ ወልዲያን መልሶ ለማቋቋም 54 ሚሊዮን ብር መደበ

ገጽ 4

# ቢሮው በ6 ወሩ ከ284 ሺህ በላይ ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፈጠሩን ገለፀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት በስድስት ወራት 284 ሺህ 978 ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፈጠሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

ቢሮው የ2015 በጀት ዓመት የስድስት ወር እቅድ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ በተመለከ ትላንትና ውይይት አካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ እንደገለጹት፤ በግማሽ ዓመት 200 ሺህ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ284 ሺህ 978 ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

በቀጣይ ስድስት ወራትም የሥራ ዕድል ፈጠራውን ለማሳደግ አስፈላጊው ክንውን እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

በከተማዋ የሥራ ዕድል ልህቀት፣ ምርትና ምርታማነት የማሻሻል ሥራ እና ሰላማዊ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት መፍጠር ዋነኛ የትኩረት መስኮች ተደርገው እየተሠሩ መሆኑን አስታውሰዋል።

የቢሮው እቅድ ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዘላለም ወጋየሁ በበኩላቸው፤ የቢሮው የትኩረት መስክና ስድስት ወር እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለውይይት አቅርበዋል።

የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ፣ በሥራ ቦታ ደህንነት እና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ዋነኛ የቢሮው የትኩረት መስክ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

በበጀት ዓመቱ 400 ሺህ አማራጭ የሥራ ዕድሎች ለመለየት ታቅዶ 438 ሺህ 590 የሥራ ዕድሎች መለየታቸውን ገልጸዋል።

በስድስት ወራት ውስጥ 375 ሺህ ሥራ ፈላጊዎች ተለይተውም ለ319 ሺህ የሥራ ፈላጊዎች የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል።

በተጨማሪም 58 ሺህ 688 ሥራ ፈላጊዎች የቴክኒክና ሙያ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ መደረጉን ገልጸዋል።

በስድስት ወር ውስጥ 3 ሺህ 611 አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን ለማደራጀት ታቅዶ 2 ሺህ 476ቱን በማደራጀት 68 በመቶ አፈፃፀም መመዝገቡን አስታውቀዋል።

ከኢንተርፕራይዞቹ መካከል 847ቱ በኢንዱስትሪ ዘርፍ፣ 371ዱ በከተማ ግብር ዘርፍ እንዲሁም 1 ሺህ 258ቱ ደግሞ በአገልግሎት ዘርፍ የተደራጁ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በስድስት ወራቱ ለ51 አዲስ እና 128 ነባር ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፍቃድ እና የፍቃድ እድሳት መስጠቱንም ተናግረዋል።

አቶ ዘላለም እንዳስታወቁት፤ የቢሮው ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች የሥራ ዕድል ፈጠራን ለማሳደግ የሚረዱ የመረጃ ሥርዓቶችን ማዘመን እንዲሁም የኅብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥራዎች ናቸው።

ፎቶ፡- በገበየሁ ገብሬ



አቶ ጃንጥራር አባይ



አቶ ዘላለም ወጋየሁ



# “የካርል አደባባይ የትራፊክ መጨናነቅ በ10 ቀናት ውስጥ ይቀረፋል”

**- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ**

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በካርል አደባባይ አካባቢ ያለውን የትራፊክ መጨናነቅ በ10 ቀናት ውስጥ ለመቅረፍ የትራፊክ መብራት የመተካት ሥራ እያከናወነ እንደሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ፤ ኤጀንሲው የትራፊክ ፍሰትን ለማሻሻል የካርል አደባባይን በመብራት የመተካት ሥራ እያከናወነ እንደሆነ አስታውቋል።

የመብራት ተከላ ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ አደባባይ እያለ በቦታው ላይ በተለይ ጠዋት እና ከሰዓት እስከ 10 ደቂቃ ይፈጅ የነበረው የመንገድ ላይ የቆይታ ጊዜን ወደ ሦስት ደቂቃ ለመቀነስ ከማገዙም በላይ የእግረኞች እና የአሽከርካሪዎችን ደህንነት የተሻለ እንዲሆን ያደርጋል ሲል ኤጀንሲው ገልጿል።

ኤጀንሲው በካርል አደባባይ ላይ የነበረውን ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ችግር ለማወቅ ባደረገው ጥናት አደባባዩን ጠዋት እና ከሰዓት ለማለፍ እስከ 10 ደቂቃ እንደሚፈጅና ችግሩን ለመቅረፍ ወደ ተግባር መግባቱን እንዲሁም ኤጀንሲው ችግሩን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየሠራ መሆኑን በላከው መግለጫ አስፍሯል።

እንደ መግለጫው፤ ባለስልጣኑ አደባባዩን በማፍረስ የአስፋልት ንጣፍ ሥራውን ያከናወነ ሲሆን የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ደግሞ የትራፊክ መብራት ተከላ፣ የትራፊክ ምልክት ተከላ፣ የቦላርድ ተከላ የመንገድ አካፋይ እና የዜብራ ቀለም ቅብ፣ የእግረኛ ደህንነት የሚያስጠብቁ ሥራዎችንና የመንገድ አጠቃቀም ሥርዓትን የመወሰን ሥራ ይሠራል።

በዚህም በአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በኩል አደባባዩን የማፍረስ፣ የሙሌት እና የከርብ ስቶን ሥራ እየተጠናቀቀ ሲሆን በኤጀንሲው በኩል ደግሞ ለትራፊክ መብራት የሚሆን የኮንዲውት ቀበራ ሥራ መጠናቀቁን አስታውቋል።

የመብራት ቋሚ የሚተከልበት ቦታ ቁፋሮ እና የፋውንዴሽን እንዲሁም የደህንነት ማስጠበቂያ ሥራዎች በመከናወን ላይ የሚገኙ ሥራዎች ሲሆኑ አጠቃላይ ሥራውን በ10 ቀናት ለማጠናቀቅ እየተሠራ እንደሚገኝ በመግለጫው ተመላክቷል።

ኤጀንሲው የትራፊክ ፍሰቱ በትራፊክ መብራት እንዲስተናበር ከተደረገ በኋላ የትራፊክ ፍሰቱ ሁኔታ እየታየ እና የትራፊክ ቆጠራ እየተወሰደ ፍሰቱን ለማሳለጥ እና ተቀባይነት ያለው ለማድረግ በየጊዜው የትራፊክ መብራት ሰዓት ኦፕትማይዜሽን ሥራን የሚያከናውን እንደሆነም ተገልጿል።

ኤጀንሲው ከዚህ በፊትም አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ የተለያዩ ማሻሻያዎችን በማድረግ ተጨባጭ ለውጦችን ያስመዘገበ ሲሆን ለአብነት የጦር ኃይሎች፣ አፍሪካ ኅብረት፣ አየር ጤና እና የጎሮ አደባባዮች ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ በቀጣይም ማሻሻያ ሊደረግባቸው በጥናት ከተለዩ አደባባዮች እና ወደ መብራት ከሚቀየሩት አደባባዮች መካከል ጀርመን አደባባይ አንዱ ነው፡፡

# ሕንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ መንግሥት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ ከተሞች የሚሠሩ ሕንፃዎች አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ አለመሆናቸውን የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌደሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባይነህ ጉጆ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በሀገራችን የተሠሩት ሕንፃዎች ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ አይደሉም።

ነባር ሕንፃዎችን ስንመለከት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆነ አሳንሰርም ሆነ ደረጃ አልባ መወጣጫ የላቸውም። ይህ ለምን ሆነ ብለን ስንጠይቅ የቆዩ ሕንፃዎች መሆናቸው እንደምክንያት ይነሳል ሲሉ ተናግረዋል።

ትክክለኛ ችግሩ የቆዩ ወይም አዲስ መሆናቸው ሳይሆን ትኩረት የመስጠትና ያለመስጠት ችግር ነው ያሉት አቶ አባይነህ፤ በቅርቡ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ፈሶበት የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት እድሳት ተደርጎለታል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን አካል ጉዳተኞች የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ትያትር ቤት ገብተው አንዳንድ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም ሲሉ ገልፀዋል።

በአዲስ አበባ በየወረዳዎቹ ከ100 ያላነሱ ጤና ጣቢያዎች መኖራቸውን በማንሳትም እነዚህ ጤና ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆናቸውን አብራርተዋል።

ትምህርት ቤቶችም ቢሆኑ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ እንዳይደሉ ያብራሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ባለፈው ዓመት መጨረሻ በ2015 ዓመት ፈቃድ ለመስጠት ሁሉም የግል ኮሌጆች መሠረተ ልማቶቻቸው የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ማድረግ እንዳለበት ደብዳቤ ጽፎ የነበረ ቢሆንም ተደራሽ ማድረጋቸው ሳይረጋገጥ ፈቃድ እየተሰጠ እንደሚገኝ አንስተዋል።

መንግሥት ተገቢውን ኃላፊነት በመውሰድ ለአካል ጉዳተኞች የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማስፈጸም እንደሚኖርበት አመላክተዋል፡፡

አቶ አባይነህ እንደገለፁት፤ አብዛኞቹ ትልልቅ የፌዴራል ተቋማት የሚሠራቸው መሠረተ ልማቶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አይደሉም ሲሉም በርካታ አብነቶችን በማንሳት አስረድተዋል። በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሕንፃዎችን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ሰፊ ችግሮች እንደሚስተዋሉም አክለው ገልጸዋል፡፡

የመሠረተ ልማቶች ምቹ አለመሆን የአካል ጉዳተኞችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ይቀንሳል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ መንግሥት ለሁኔታው ትኩረት በመስጠት የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ሊያሳድግ ይገባል ብለዋል፡፡

በአሁን ወቅትም መሠረተ ልማቶች ከንድፍ ጀምሮ የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽነት አረጋግጦ በትኩረት የሚሠራ ተቋም አለመኖሩን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ ተቋማት የሚሠሩትን ሕንፃ ንድፍ አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን አሠራር መዘርጋት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት በሀገሪቱ የሚኖሩ የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር በትክክል አውቆ በመሠረተ ልማቱ ዘርፍ ትክክለኛ እቅድ ተይዞ መሥራት መቻል አለበት ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለውጡ ከመጣ በኋላ የታዩ መሻሻሎች መኖራቸውን ጠቅሰው መሠራት የሚገባቸው ነገሮች ከኅዘኔታ አንፃር ሳይሆን፤ ፖለቲካዊ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራ እንደሚገባ ገልፀዋል።



አቶ አባይነህ ጉጆ

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሀገር አቀፍ ፈተናው የታየው የፈተና ውጤት ውድቀት ብቃት ሳለው ዜጋ ማፍሪያ የከፍታው መነሻ እንዲሆን በቀጣይነት ይሠራ

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት በንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት እንደተጀመረ የታሪክ ልሳናት ይጠቅሳሉ። ከዚያን ዘመን ጀምሮ ትውልዶችን በዘመናዊ ትምህርት በማነጽ ሀገርን ወደ ተሻለ የሥልጣን ምዕራፍ ለማሻገር ሰፊ ጥረቶች ተደርገዋል። ይብዛም ይነስም የተገኙ ወጤቶች ሀገር ከትናንት ዛሬ የተሻለች እንድትሆን ረድቷል።

በተለይም ከነጻነት ማግስት ጀምሮ ዘመናዊ ትምህርትን በመላው ሀገሪቱ በማስፋፋት፤ ሀገርን የዘመናዊ ስልጣኔ ተቋዳሽ ለማድረግ የተሄደበት ርቀት፤ የተገኘው ውጤትም ከፍያለ እንደነበር ብዙዎች ይስማማሉ። በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የለፉና የእድሉ ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎችም በብዙ መልኩ የሀገር ባለውለታ በመሆን ተጠቃሽ ናቸው።

ደርግ ወደ ሥልጣን እስከመጣበት ጊዜ ድረስ የነበሩት ጊዜያት ትምህርትን በመላው ሀገሪቱ ለማዳረስ ከፍያሉ ጥረቶች የተደረጉበት፤ አበረታች ውጤቶችም የተመዘገቡባቸው ነበሩ። ደርግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላም ትምህርትን በስፋት ለመላው ሕዝብ ለማዳረስ ከመሠረተ ትምህርት ጀምሮ ረጅም ርቀት ተጉዟል። ያስመዘገበውም ውጤትም በትምህርት ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ከመሆኑም ባሻገር ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸረው መሆኑን አይዘነጋም።

የኢሕአዴግ መንግሥትም ቢሆን በተለይም የከፍተኛ ትምህርትን ለማስፋፋት በስፋት የዩኒቨርስቲዎችን ግንባታ በማካሄድ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ወደ ዩኒቨርስቲ ገብተው የሚማሩበትን፤ የግል ዩኒቨርሲቲዎችም በስፋት ወደ ዘርፉ የሚቀላቀሉበትን እድል ፈጥሯል። በዚህም ሀገሪቱ ብዛት ያላቸው የዩኒቨርስቲ ምሩቃን እንዲኖራት አስችሏል።

በዚህ ትምህርትን በስፋት የማዳረስ ሂደት ውስጥ ሀገርን ያጋጠማትና በየጊዜው አቅም እየገዛ መጥቶ ዛሬ ላይ ሀገርን በአደባባይ እንደ ሀገር የፈተነው የትምህርት ጥራት ጉዳይ ነው። በየወቅቱ /አንድ የፖለቲካ ሥርዓት መጥቶ በሄደ ቁጥር/ በትምህርት ሥርዓት ላይ የሚደረግ ለውጥ፤ ለውጡ ከትምህርትና ከጥራቱ ይልቅ ፖለቲካን ታሳቢ ማድረጉ በሀገሪቱ በተሻለ መነቃቃትና ተስፋ የተጀመረው ዘመናዊው ትምህርት ጥራቱ ተጠብቆ የሚፈለገውን ያህል ብዙ ርቀት መሄድ ሳይችል ቀርቷል ።

በየወቅቱ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች ፤ ዘመናዊ ትምህርት እንደ አንድ የለውጥ መሣሪያ ሕዝብና ሀገርን በመለወጥ፤ ለዜጎቿ የተሻለች ሀገር ከመፍጠር ይልቅ ፤ዘመናዊ ትምህርት እራሱ ችግር ውስጥ ወድቆ/በሕይወትና በሞት መካከል ሆኖ/የሚታደገው የሚፈለግበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አስገድደውታል። ለዚህ ደግሞ የሰሞኑ የ12 ክፍል መልቀቂያ ፈተና ትክክለኛ ማሳያ ነው።

የትምህርት ሚኒስትር ከትናንት በስቲያ ይፋ እንዳደረገው ከ2014 የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ተፈታኞች መካከል ከ50 በመቶ በላይ ያመጡት ተፈታኞች ሦስት ነጥብ ሦስት በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ መደበኛ ተፈታኞችን ካስፈተኑ 2959 ትምህርት ቤቶች መካከል 50 በመቶ እና ከዚያ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት አንድ ሺህ 798 (60.76 በመቶ) ሲሆኑ፤ አንድ ሺህ 161 (39.24 በመቶ) ትምህርት ቤቶች ግን በሀገር አቀፍ ፈተናው አንድም ተማሪ ማሳለፍ አልቻሉም። ይህ እውነት ችግሩ የቱን ያህል የከፋ እና አስደንጋጭ እንደሆነ በተጨባጭ ማሳየት ያስቻለ ክስተት ነው።

የትምህርት ጥራቱ ችግር እንዳለ ሆኖ ስርቆት እና ኩረጃ አስከፊ ደረጃ በመድረሱ የአሁኑ ፈተና በዩኒቨርሲቲዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የፈተና አሰጣጡ ከዚህ ቀደም ከነበሩት የተለየና በሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ርብርብ በስኬት የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ውጤቱ ግን ለዓመታት ሲንከባለል የቆየ የበርካታ ችግሮች መገለጫ እና ተሸፍኖ የቆየውን እውነተኛ የትምህርት ሥርዓት ያለበትን ደረጃ ያመላከተ ነው።

ሚኒስቴሩ ቀደም ባለው ጊዜም ቢሆን በኢትዮጵያ ካሉ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች 65 በመቶ የሚሆኑት ማንበብ እንደማይችሉ፣ የሚያስተምሩትን ትምህርት ከተፈተኑ መምህራን መካከል 85 በመቶ የሚሆኑት ብቁ አለመሆናቸውን፣ 99 በመቶ የሚሆኑት ትምህርት ቤቶችም አስፈላጊውን መስፈርት እንደማያሟሉ ማስታወቁ ይታወሳል።

ይህ ከታች የሚጀምረው ሀገራዊ የትምህርት ጥራት ችግር ፤አሁን ባለው ሁኔታ በአስራ ሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ጎልቶ ይውጣ እንጂ በየትምህርት ክፍሉ የሚሠጡ ፈተናዎች በተገቢው ጥንቃቄና ቁጥጥር ተግባራዊ ቢሆኑ ከዚህ የከፋ ውጤት ሊመዘገብ እንደሚችል አይጠረጠርም።

ከዚህም ባለፈ በቀጣይም በዩኒቨርስቲዎች አካባቢ የመውጫ ፈተና ለመስጠት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል የተያዘው ፕሮግራም ተግባራዊ ሲሆን፤ ምናልባትም ከዚህ የከፋ ነገር ይዞ ስላለመምጣቱ መተማመኛ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ የለም።

ትምህርት የአንድን ሀገር እና ሕዝብ ዕጣ ፈንታ ከመቀየር አንጻር ካለው ሁለንተናዊ አስተዋጽዖ አንጻር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጀመረው የትምህርት ሥርዓቱን የማከም ሥራ ሀገርንም ሆነ ተቋሙን ከፍያለ ዋጋ ማስከፈሉ የማይቀር ነው።

ይህንን የገነገነ ፈታኝ ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት ሚኒስቴሩ የጀመረው ጥረት ፤ ከፍ ያለ ቁርጠኝነት የሚታይበት ፤ እያስመዘገበም ያለው ውጤትም ተስፋ የሚጣልበት ፤ ሊበረታታና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ይህ በትምህርቱ ዘርፍ ሀገርን እንደ ሀገር ለመታደግ የተጀመረው ፈታኝ ሥራ የሁሉንም ዜጋ ርብርብ የሚሻ ፤ በአንድ ትምህርት ሚኒስቴር ጥረት ብቻ ከዳር ይደርሳል ፤ የተበላሸው ይቃናል፤ የወደቀው ይነሳል ብሎ ለማሰብ የሚቀል አይደለም! ።

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# በጎነት በሁሉም ዜጎች፣ሁሌም ቢሆን

**ስምስም መንግሥቱ**

የምንገኝበት የጥር ወር ማኅበራዊ ይዘት ያለው መንፈሳዊ በዓላትን ብቻ ሰይሆን የሠርግ ወቅትም ጭምር በመሆኑ አብሮነት፣መተጋገዝ፣መተሳሰብ በአጠቃላይ የሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ይበልጥ የሚጠነከርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከክርስቶስ ልደት(ገና)በዓል ቀጥሎ የተከበረው ጥምቀት የአደባባይ በዓል(ፌስቲቫል)በመሆኑ ማኅበራዊ መስተጋብሩ ጎልቶ ይታያል፡፡

ከቤተሰብ አልፎ ጎረቤትና ወዳጅ የሚታደምበት የሠርግ ሥነሥርዓትም ቢሆን አብሮነት የሚጠናከርበት ነው፡፡ በዚህ አብሮነት ጎልቶ በሚታይበት ወር ሰዎች በየአደባባዩ ያሳዩትን ትሕትና አይተንበታል፡፡ በዚህ መልኩ የሚደምቀውን የጥምቀት በዓል ለመታደም ከባሕር ማዶ ሳይቀር የሚመጡ እንግዶች ሲማረኩም እናያለን፡፡ በአንደበታቸውም ሲመሰክሩ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች እንሰማለን፡፡

ባሳለፍነው የጥምቀት በዓል በተለይም የወጣቶች በጎ ሥራና ትሕትና የጎላ ነበር፡፡ ቀናነታቸው ለእምነታቸው ብቻ አልነበረም፡፡ ከእምነቱ የሚጠበቀውን በጎነት በተግባር ለማዋል በበዓሉ ድካም የተሰማቸው ከድካማቸው እንዲበረቱ እግር አጥበውና አሽተው ትሕትናቸውን ያሳዩ ወጣቶችን ለማየት ችለናል፡፡ካየሁትና ከታዘብኩት ጎልቶ የወጣውን እንዲህ ለአብነት ጠቀስኩ እንጂ ወጣቶቹ ከማስተናበር ጀምሮ ያጋጥማሉ ተብለው ቀድሞ በስጋት ጥንቃቄ ሲደረግ የነበረውን ሁሉ ለመከላከል ዝግጁ ከመሆን ጀምሮ በትሕትና የተለያዩ በጎ የሆኑ ተግባራትን ፈጽመዋል፡፡

ውድ አንባቢያን ታዲያ ምን አዲስ ነገር አለ በዚህ ወቅት በጎ ተግባሩ ሁሌም የተለመደ ነው ትሉ ይሆናል፡፡ የተለመደውን ልነግራችሁ ሳይሆን የተለመደውን በበዓል ጊዜ የምናየውንና የምናሳየውን ትሕትና እና አብሮነት በሌላ ጊዜ ወይንም በአዘቦቱ ለምን አናየውም? በሚለው ላይ ነው ትኩረቴ፡፡

በግሌ በበዓላት ወይንም አንድ ክስተት ሲኖር ያ ኩነት እስኪያልፍ ብቻ በተወሰኑ አካላት ብቻ የሚከናወኑ በበጎነት የሚገለጹ ነገሮች በቂ ናቸው ብዬ አላስብም፡፡ በሀገር ደረጃ የሚገለጽ በሁሉም ዜጎች መልካምነት መኖር አለበት ባይ ነኝ፡፡ የበጎነቱ ተግባርም ከወጣቶች ብቻ ሳይሆን ታዳጊዎችን ጨምሮ ከጎልማሶችና ከአረጋውያን በአጠቃላይ የዜጎችም ኃላፊነት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

ችግሮችን ወይንም ነገሮችን የአንድ አካል ብቻ አድርጎ መውሰድ፣ግለኝነት፣ምን አገባኝ፣ምንቸገረኝ የኢትዮጵያውያን መገለጫ አይደለም፡፡ እንደውም ከራሱ የሌላውን ጉዳይ እንደራሱ አድርጎ ችግሩን ሲጋራ፣ደስታና ኃዘንን በጋራ ሲወጣ ነው የሚታወቀው፡፡ግለኝነትን ስላልኖርንበት ቃሉንም የምናውቀው በንባብ ወይንም በምዕራቡ ሀገር ከኖሩ ተሞክሮ ካላቸው ሲነገር ነው፡፡

በምዕራቡ በአብዛኛው ግለኝነቱ የበዛ በመሆኑ እርስበርስ ላለው ግንኙነት ግዴለሽነቱ የበዛ እንደሆነና የሚፈፀመው ወንጀልም ከዚሁ የመነጨ እንደሆነም ሲነገር እንሰማለን፡፡ አንድ ታዳጊ አብረውት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የጥይት ሩምታ አዘነበ የሚለው ወሬ አዲስ አይደለም፡፡

ማኅበራዊ ቀውስ ያስከተለው የግለኝነት ችግር እንደሆነም በጥርጣሬ ከሚነሱ ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳል፡፡ በኢትዮጵያም አንዳንድ ወጣ ያሉ ድርጊቶችን ሳይ ከዚህ ጋር ይመሳሰልብኛል፡፡ ምናልባት ይሄ ግሎባላይዜሽን ወይንም ዓለም አንድ መንደር እየሆነች ነው የሚለው እያሳሳተን ይሆን?ብዬ አስባለሁ፡፡

የበጎነት መገለጫ የሆኑ ተግባሮችን ለአንድ ወቅት ክስተት ካየን በኋላ በሌላ ጊዜ ሲደገም አለማስተዋሌ ጥያቄ ይፈጥርብኛል፡፡ በወጣቶቹ ትሕትና እና መልካም ተግባር ተደስቶ ምርቃቱንና ምስጋናውን ሲያሽጎደጉድ የነበረው ማኅበረሰብም መልካም ነገር በተናገረው አንደበቱ መልሶ እርግማንና ነቀፌታውን ሲያዥጎደጉድ ይሰማል፡፡

ይሄ ለምን ሆነ?አንድ ተንቀሳቃሽ ስልክ ለመቀማት በወገን ላይ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ሲፈጸም ያ ትሕትና የተሞላበት በጎነት የት ገባ? ያስብላል፡፡ በየትራንስፖርቱና በተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች ያለው መከባበርና መተሳሰብ ኢትዮጵያውያንን በሚገልጽ መልኩ ሆኖ የማላገኝባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ፡፡

እንዲህ ያሉ ማኅበራዊ መስተጋብሮች ገንዘብ አይጠይቁም፡፡ ቅን ልቦና፣ሰፋ ያለ አዕምሮና ሰብዓዊነት ብቻ ነው የሚያስፈልገው፡፡ በገንዘብ አቅም ያጣውንም ቢሆን ዛሬ የኑሮ ውድነቱ አላፈናፍን ቢልም ‹‹ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ደግሞ ጌጡ›› በሚባለው ብሂል መወጣት የሚቻልበት ዕድል አለ፡፡ ዋናው ‹‹ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም›› እንደሚባለው ፍላጎት ነው የሚያስፈልገው፡፡

እንዲህ ያለው ነገርም እየደበዘዘ ነው ባይ ነኝ እኔ፡፡ የዳር ተመልካች መሆንም ሌላው የታዘብኩት ጉዳይ ነው፡፡ እንከኖች ቢኖሩም በዚህ ውስጥ ተሆኖ በሀገር ውስጥ የሚሠራው የልማትም ሆነ ሌላ ሥራን ገንቢ በሆነ መልኩ ሳይሆን የሚያጣጥል ትችት ጎልቶ ይታያል፡፡እንደዜጋ ያገባኛል ከሚለው ምን አገባኝ የሚለው ጎልቶ ይስተዋላል፡፡

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማኅበራዊ ግንኙነታችን እና በኢኮኖሚ ላይ በእያንዳንዳችን ላይ ተጽዕኖውን ያሳረፈብን ኢትዮጵያን ከውስጥም ከውጭም ገጥሟት የነበረው ፖለቲካዊ፣ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናንም ጉዳያችን ያደርግነው ስንቶቻችን ነን? የሚለውንም ጉዳይ ብናይ እንዲሁ ለጉዳዩ ሩቅ የመሆን ነገር ነው የታዘብኩት፡፡

ለዚህም በየማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉት መረጃዎች ማሳያ ናቸው፡፡ ሁለተኛ ዜግነት በያዙ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን፣በሀገር ውስጥም ሆነው ጉዳዩን የሌላ ሀገር አስመስለው ሲያቀርቡ ይሄ ያገባኛል የኔ ጉዳይ ነው የሚለው ኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ እየራቀ እንዲሄድ፣የፖለቲካ ጽንሰ ሀሳቡ በሚፈቅደው ሀገራዊ ይዘትን ሳይለቅ ከሚሰጠው ትችት ፈር የለቀቀ ሆኖ እንዲሰማኝ ነው ያደረገኝ፡፡

እንደውም የወሬ አጀንዳ በማድረግ የገቢ ምንጭ ነው የሆነላቸው፡፡ ማኅበራዊ ድረገጾች ዛሬ ለጋዜጠኝነት በአቋራጭ መክበሪያ ሆኗልም እየተባለ ነው፡፡ ለሙያቸውና ሙያቸው ብቻ ጊዜ ሰጥተው ጥሪት ሳይኖራቸው፣በኑሯቸውም እልፍ ያለ ነገር ሳያገኙ የጋዜጠኝነትን ሥነምግባር ባልተከተለ፣ለሀገርና ለዜጋ ቦታ ሳይሰጥ ገንዘብ ተኮር መረጃ በማስተላለፍ ለዛሬ ብቻ ባደሩት ሲቆጩና ሲበሳጩ ይስተዋላል፡፡

የትችት ናዳ እየወረደባቸው እራሳቸውን ለማስተካከል ፍቃደኝነቱ የሌላቸው ለመሳሳት ዝግጁ የሆነ በማግኘታቸው ነው የሚሉም አልጠፉም፡፡ ይኸው ማኅበራዊ ድረገጽ ላይ ተብሷል ብለው የሚከራከሩ ያጋጥማሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን የሚታወቁት ‹‹ነገርን ከሥሩ፣ውሃን ከጥሩ›› በሚል አባባላቸው ነው፡፡

ለውሳኔ ሳይቸኩሉ፣ነገሮችን ለማመዛዘን፣ክፉና ደጉን ለመለየት ጊዜ የመስጠት የቆየ እሴት አላቸው፡፡ እንዲህ ያሉ መልካም ነገሮች ለአንዳንድ ዓላማዎች የሚውሉባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩም ዘላቂ ባለመሆናቸው ወጥነታቸውን እናጣለን፡፡



አቶ ዱባለ አብራሬ

# ክልሉ ወልዲያን መልሶ ለማቋቋም 54 ሚሊዮን ብር መደበ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ: አማራ ክልል ወልድያ ከተማን መልሶ ለማቋቋም 54 ሚሊዮን ብር መበጀቱን የከተማዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የከተማዋ አስተዳደር ተቀዳሚ ከንቲባ አቶ ዱባለ አብራሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ከተማዋ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ከባድ ውድመት የደረሰባት ሲሆን ከተማዋን መልሶ ለማቋቋም የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከተማዋን መልሶ ማቋቋም በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የገለጹት ከንቲባው፤ የክልሉ መንግሥት ወልዲያን መልሶ ለማቋቋም 54 ሚሊዮን ብር ከመበጀቱ በተጨማሪ በቴሌ ቶን ገቢን በማሰባሰብ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች ለማከናወን የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጡንም ጠቁመዋል፡፡

በተለይ የሪጅፖሊታንትነት ከተማ ደረጃን የሚመጥኑ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች እና የወጣቶች ማዕከላትን ለማስገንባት የመሠረት ድንጋይ በማስቀመጥ ለግንባታቸው ሰፊ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ያብራሩት ከንቲባው፤ የፕሮጀክቶች ግንባታ በተያዘላቸው ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ የአዳዲስ ተጨማሪ ፕሮጀክቶች ግንባታ ለማስጀመር እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ለመልሶ ግንባታው የገቢ ምንጭ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ገቢን የማሰባሰብ ሥራ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ዱባለ፤ አዲስ አበባ ከሚኖሩ የአከባቢው ተወላጆች እና ወዳጆች ገቢን በቴሌ ቶን መንገድ ለማሰባሰብ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

ገቢን በተገቢው መንገድ በማሰባሰብና ለተፈለገው የመልሶ ግንባታ ዘጠኝ አባላት ያለው ኮሚቴ በማዋቀር አመራር ተመርጦ ወደ ሥራ መግባት መቻሉንም አቶ ዱባለ አብራርተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ ለከተማዋ አምባሳደር ሆነው የተሾሙት ኢንጂነር ዶክተር አረጋ ይርዳው ከኬጂ ጀምሮ ፋሚሊ ጎልደን ዩኒቨርሲቲ በከተማዋ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ የማስቀመጥ ሥራ መሥራት እንደተቻለ አስታውቀዋል፡፡

ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠባቸው ፕሮጀክቶች ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ እና የከተማዋን ገጽታ ለመቀየርና እድገቷ እንዲፋጠን ለማድረግ የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ የጎላ በመሆኑ ግንባታቸው እንዲፋጠን በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የሕዝብን ተስፋና ተጠቃሚነት ለመመለስ የሚያስችሉ በመሆናቸው ኅብረተሰቡን በማስተባበር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የተጀመሩት ፕሮጀክቶችም ቢሆን የከተማዋን የዕድገት ደረጃ የሚያሳዩ በመሆናቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባ አቶ ዱባለ አሳስበዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ፕሬስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ35 በመቶ ብልጫ አለው ብለዋል፡፡

የድርጅቱ ደንበኞች እርካታ 92 በመቶ፤ የሠራተኞች እርካታ ደግሞ 91 በመቶ ነው ያሉት ወይዘሮ ሔለን፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሁሉም ተግባራት በአጠቃላይ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት አፈፃፀሙ 91 ነጥብ 19 በመቶ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ምክትል ዋና ሥራአስኪያጇ አክለውም፤ የሕትመት ወረቀት በመወደዱ የተነሳ የማተሚያ ቤት ዋጋ መጨመር የጋዜጣ ቅጂ መጠን በሚፈለገው ልክ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኗል፡፡ ተቋሙ የራሱ ማተሚያ ቤት እንዲኖረው፣የበጀት ድጎማ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መሆናቸውን ለዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት አስረድተዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ጋሻው ዳኘው በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የተከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች ለውጥ ያመጡ ናቸው፣ለውጡም ተግባራዊ እንደሆነ ተቋሙን በጎበኘንበት እንዲሁም በስድስት ወራት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ተገንዝበናል ብለዋል።

የምርምር ጋዜጠኝነት ላይ ይበልጥ መሥራት እንዲሁም ድርጅቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ከሚያከናውናቸው የሚዲያ ሥራዎች በተጨማሪ ከክልሎች ጋር በመነጋገር በሌሎችም ቋንቋዎችም በመሥራት ተደራሽነትን መፍጠር እንዳለበት ተናግረዋል።

የቋሚ ኮሚቴው አባል ዶክተር አንጋሳ አህመድ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አካታች የሆነ ታሪክን በመሰነድ ታሪክን ያዳነ፤ ሀገርን እያስቀጠለ ያለ ተቋም ነው፤ተቋሙ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ጉዞ ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላኛው የቋሚ ኮሚቴው አባል አቶ ተመስገን አምባቸው በበኩላቸው፤ የባለፉት ስድስት ወራት የኢፕድ የሥራ አፈፃፀም ሙያን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደተመራ እንደሆነ ተረድቻለሁ፤የተሞክሮ ማዕከል እየሆነ ነው፤ ይህንን ማስቀጠል አለበት ነው። የተቋሙን ቁልፍ ችግሮች ለመፍታት እንሠራለን ብለዋል።

የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል ወይዘሮ አቡኔ ዓለም ኢፕድ ባለፉት ስድስት ወራት ተጨባጭ ለውጦችን ማስመዝገቡን ገልጸው፤ ለሥራ ምቹ ያልሆኑ ሕጎችን በማሻሻል ድጋፍና ክትትል እናደርጋለን ሲሉ ገልጸዋል።

የኢፕድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ የተቋሙ የአስር ዓመት እቅድ በአዋጅ ከተሰጠው ኃላፊነት አንፃር ከሀገሪቱ የአስር ዓመት እቅድ የተቀዳ ነው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሙያ ፣ቋንቋ ፣ሥነጽሑፍ እንዲሁም ታሪካዊ ጥናትና ምርምር ላይ ይሠራል። የመፈፀም አቅማችን እያደገ ሲሄድ በተለያዩ የሀገርና የውጪ ቋንቋዎች እንሠራለን ብለዋል።

ለአሠራር የማይመቹ ሕጎች ቢሻሻሉ፣ማተሚያ ቤት የማቋቋም እቅዳችን እውን ቢሆን ሀገር የሚመጥን ተቋም ከዚህም በላይ እንገነባለን ሲሉ አቶ ጌትነት አስታውቀዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ እውነቱ አለነ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባለፉት ስድስት ወራት ተጨባጭ ለውጦች ማስመዝገቡን ገልፀው ተቋሙን መደገፍ የቦርዱም ይሁን የቋሚ ኮሚቴው ታሪካዊ ኃላፊነት ነው ብለዋል።

አቶ እውነቱ እንደገለፁት፤ ድርጅቱ በተለይም የኢትዮጵያን ታሪክ በመሰነድ፣ በገቢ አሰባሰብ፣የብራንዲንግ ሥራዎች፣ የይዘት ማሻሻያ ተግባራት ለተቋማዊ የለውጥ ሥራዎቹ ተጠቃሽ ናቸው።

ተቋሙ የሕትመት ሚዲያ እንደመሆኑ መጠን ውስብስብ ችግሮች ስላሉበት ከበጀት ቋሚ ኮሚቴ ጋር በመነጋገር ችግሮች ይፈታሉ ብለዋል፡፡

ከግማሽ ዓመት የክንውን ሪፖርት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከምሥረታው ጀምሮ እስከ አሁን ያለው ጉዞ እንዲሁም የተቋሙ የአስር ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ለዴሞክራሲ በጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ቀርቧል፡፡

# በአስር ዓመታት ለ20...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሚረዱ የዝግጅት ምዕራፍ ፣ የሪፎርም አፈጻጸም ፣ ዓብይ ትግበራዎችና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል።

ዜጎች መንግሥት በመደበው አራት ቢሊዮን ብር ተጠቅመው ሥራ እንዲፈጥሩና ሃብት እንዲያፈሩ ይደረጋል። ይህም ምርታማነትን በማሳደግ የማይክሮ ኢኮኖሚውን ውጤታማ እንደሚያደርግ ይታመናል ብለዋል።

በእስካሁኑ አፈጻጸም በጎ ውጤት ታይቷል፤ በ2015 በጀት ግማሽ ዓመት የታየው የሥራ አፈጻጸም ቀጣይ እቅዱን ለማሳካት የሚያስችል ነው ያሉት አቶ ንጉሡ፤በግማሽ ዓመቱ ለ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ሥራ ዕድል ፈጠራው ከባለፈው ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር በ527ሺህ ሥራ እድሎች ፈጠራ ብልጫ እንዳለው ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ከሆነ፤ ኦሮሚያ ፣ አማራና አፋር በሥራ ዕድል ፈጠራ የተሻለ አፈጻጸም አስመዝግበዋል፡፡ በኦሮሚያና አማራ ክልል ያለው የበጋ ስንዴ ግብርና ምርትና ምርታማነት መጨመር ለሥራ ዕድሉ ማደግ ማሳያ ነው፡፡

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ በበኩላቸው፤ የፋይናንስ አቅርቦት ፣ የሥልጠና አማራጭ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ስምሪት መጓደል ችግሮች መሆናቸውን አንስተዋል።

በተጨማሪ ጥራት ያለው መረጃ ፍሰትና ለሥራ ዕድል ፈጠራው ይበልጥ እንዳያድግ ውስንነት ይፈጥራሉ። ችግሮቹን በመቅረፍ የ10 ዓመት ዕቅዱን ማሳካት ይገባል ብለዋል፡፡

በሥልጠና ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ አሠሪና ሠራተኛ ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥነምሕዳሩን የማመቻቸት ክንውኖች እንደሚጠናከሩ ገልጸው ፤ በዘርፉ የታዩ ጠንካራ ጎኖችን በማስፋት በተገኘው ተሞክሮ ዕቅዱን ተግባራዊ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

የ10 ዓመት ዕቅዱን መሠረት ላደረጉ ቀሪ ሥራዎች ትኩረት በመስጠት ገበያው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ለማሰልጠን ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት አለበት ብለዋል፡፡

የአማራ ክልል ሥራና ሥልጠና ቢሮ ኃላፊ አቶ አረጋ ከበደ፤ ክልሉ በዘንድሮ በጀት ዓመት አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እየሠራ ነው። እስከ ግማሽ ዓመት 326 ሺህ ዜጎች ቋሚ፣ 164 ሺህ ጊዜያዊ በአጠቃላይ ከ490 ሺህ በላይ የሥራ ዕድሎች መፍጠር ችሏል ሲሉ አስታውቀዋል።

በግብርና ፣ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፍ ላይ የተለያዩ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል ያሉት አቶ አረጋ፤ ሰፊ በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ በርካታ ሰዎች የተሳተፉባቸው ስልጠናዎች መዘጋጀታቸውን ጠቁመዋል።

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሥራ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሮቤል ጌታቸው በበኩላቸው ፤ ከተማ አስተዳደሩ በዓመት ለ17ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር አቅዶ፤ በስድስት ወር ውስጥ ለሰባት ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አስረድተዋል። :

በኢንዱስትሪና ከተማ ግብርና ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ሮቤል፤ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ብቻ 2ሺህ 500 የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል።

የስድስት ወር አፈጻጸም በተመለከተ የተደረገው አጠቃላይ ግምገማ በማይክሮ ኢኮኖሚው ውስጥ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚያስችል ተሞክሮ የተገኘበት ነው፡፡ ግምገማው ተግዳሮቶችን በመለየት ፣ ጠንካራ ጎኖች በማስፋት በቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች በቅንጅት ለመሥራት የሚረዳ ነው ሲሉ ተሳታፊዎቹ ገልጸዋል።

# የኢንዱስትሪ ዘርፉ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የራሳችንን ምርት አምርተን፣ በሀገር ውስጥ የሚያስፈልገንን ተጠቅመን ቀሪውን ኤክስፖርት የማድረግ እንቅስቃሴው ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

ሚኒስቴሩ በተለይ ሪፎርሙን ተከትሎ በርካታ ስኬቶችን እያስመዘገበ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ራሱን ችሎ መዋቀሩ ለውጤታማነቱ አንዱ መንስኤ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንደገለጹት፤ አደረጃጀቱ ቀደም ሲል ተበታትነው የነበሩትን ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ፣ ምግብና መጠጥ፣ ኬሚካል፣ ብረት እና ካይዘን የሚባሉ ስድስት ተቋማትን ወደ አንድ በማምጣት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚል እንዲዋቀሩ አድርጓል፡፡ ሁለተኛው የኢንተርፕራይዝ ልማት ነው፡፡ ይህም የሥራ ዕድል ፈጠራ ዘርፉን ከመደገፍ አኳያ ተደራጅቷል፡፡

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በምርታማነት ላይ አወንታዊ ለውጥ አምጥቷል ያሉት አቶ ታረቀኝ፣ በቀጣዮቹ አስር ዓመታት የማምረት አቅማችንን አሁን ካለበት 50 ከመቶ ወደ 85 ከመቶ ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ 11 ሺህ የሚሆኑ አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችንም ወደ ኢንዱስትሪው ለመቀላቀል እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በተለይ ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር እና ኤክስፖርት በማድረግ እንዲሁም አዳዲስ የኤክስፖርት ምርቶችን በመጨመር በስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ ኤክስፖርትን ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ እየተሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ለዚህ ስኬታማነትም ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅንጅ እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡

ዘርፉ ከብዙ ተቋማት ጋር የሚገናኝ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተለይ ከፋይናንስ ተቋማት፤

ከትምህርት ፣ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር እና ከፍትሕ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር ሰፊ ግንኙነት እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

ይህንን የቅንጅት ሥራ ለማሳለጥ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ጅምሮች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ሆኖም ይህ በትብብር መንፈስ እንጂ በሕግ የተደገፈ ባለመሆኑ ይህንን በሕግ መደገፍ እና የተጠያቂነት አሠራር የሚሰፍንበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

አቶ ታረቀኝ እንደገለጹት ኢንዱስትሪዎችን የማስፋፋት ሥራ የአካባቢውን እምቅ አቅም ታሳቢ በማድረግ ይከናወናል፤ ለአብነትም በጎንደር አካባቢ ያለውን ሰፊ የጥጥ ሃብት ለመጠቀም ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪውን በዚህ አካባቢ የማስፋፋት፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ አካባቢ ያለውን የቀርከሃ ምርት ለመጠቀም በአካባቢው በዚህ ላይ እሴት ጨምረው የሚሠሩ ፋብሪካዎች ያስፈልጋሉ፡፡

እነዚህና መሰል ሥራዎችን በማጠናከር እና ኢንዱስትሪውን በማስፋፋት በስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ለአምስት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥርም አቶ ታረቀኝ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መነሻ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ትኩረት እንዲያገኝ፣ ቅንጅታዊ አሠራሮች እንዲጠናከሩ ማድረግ እና መዋቅራዊ ሽግግርን እውን ማድረግ መሆኑን የተናገሩት አቶ ታረቀኝ፤ እነዚህ ሥራዎች ባለፈው አንድ ዓመት በከፊል ውጤት ማምጣታቸውን ተናግረዋል፡፡

ይህንን ፕሮጀክት በቀጣይ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስቀጠል፤ በአሁኑ ወቅት በፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ደረጃ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው በቀጣይ ራሱን አስችሎ በተቋም ደረጃ የማቋቋም እቅድ መኖሩንም ጠቁመዋል፡፡

በአማራና በአፋር ክልሎች በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው ኢንዱስትሪዎችንም በተመለከተ ጥናት መካሄዱን ጠቅሰው፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ከተወያዩበት በኋላ ችግሮችን ለመቅረፍ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ተናግረዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን ችግሮቹ አሁንም ሙሉ ለሙሉ ባለመፈታታቸው ጥረቱ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

ከትግራይ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተያያዘ ግን የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ችግሮቹን የሚያጠና ኮሚቴ ተዋቅሮ በመቀሌ ዙሪያ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ያሉበትን ሁኔታ የሚያጠና ቡድን ወደስፍራው ተልኮ በአሁኑ ወቅት የመጀመሪያ ዙር ጥናት ማካሄዱን ጠቅሰው በጥናቱ መሠረት በየደረጃው ችግሮቻቸውን ለመፍታት እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን ችግሮቹን ለመፍታት የአመራር ቁርጠኝነት ፣ የባለሃብቱ ተነሳሽነት እና የሁሉም ኅብረተሰብ ርብርብ ወሳኝ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት እንዲረባረቡ ሚኒስትር ዴኤታው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ አንድምታ

**(የመጨረሻ ክፍል)**

ለሀገራችን ኢትዮጵያ ነጩን ቤተመንግስት ዴሞክራቶች ይሁኑ ሪፐብሊካኖች ቢቆጣጠሩት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ብዙም ልዩነት ስለሌለው ይህ ነው የሚባል ተጠቃሚነት የሚፈጥር አይደለም። ቀደም ባሉት ጊዜያት ሪፐብሊካኖች የግብጽ ነገር እንዴት እንደሚያንዘረዝራቸው ከግብጽ ጋር በነበሩን ድርድሮች ታዝበናቸዋል። በታላቁ የሕዳሴ ግድብ የተነሳ አሜሪካ ሁለት ጊዜ ወደ ጸጥታው ምክር ቤት ሀገራችንን መጎተቷ ሳያንስ ትራምፕ የሕዳሴውን ግድብ ግብጽ ለምን በቦንብ አታፈርሰውም እስከ ማለት ደርሰው ነበር።

ወደ ዴሞክራቶች ስንመጣ ደግሞ ባለፉት ሁለት አመታት እንዴት የበረታ ጫና ያደርጉብን እንደነበር አይረሳም። ሀገራችን 15 ጊዜ በመንግስታቱ ድርጅት በተከሳሽ ሳጥን እንድትቆም የአንበሳውን ድርሻ ተጫውተዋል ፤ ሀገራችንን ለአፍሪካ አገራት ከሰጠችው ከቀረጥና ኮታ ነፃ የሆነ የገበያ እድል(African Growth and Opportunity Act /AGOA/) አግዋ አስወጥተዋል፤ ይህ አልበቃ ብሏቸው በሀገራችን ላይ ማዕቀብ ጥለዋል፤ ከዓለም ባንክና ከአለማቀፉ የገንዘብ ተቋም ልናገኘው የነበር የፋይናንስ ድጋፍ እንዲዘገይ አድርገዋል።

ይህም ሆኖ ግን ባለፉት ሁለት አመታት ፓርቲዎቹ በሀገራችን ላይ ያራመዱትን አቋም ከወጪ ቀሪ ስናሰላው ለሀገራችን ሪፐብሊካኖች ይሻላሉ። የቢቢሲው አንቶኒ ዙርከር ምርጫው ለሪፐብሊካኖች ጥሩ ሊባል የሚችል ቢሆንም የጠበቁትን ያህል ግን አይደለም። እንደ ፎከሩት ከዴሞክራቶች ጋር አንገት ለአንገት የተናነቁባቸውን ሁሉ እንደ ማዕበል ጠራርገው ማሸነፍ አልቻሉም። ሪፐብሊካኖች ባልተጠበቀ ሁኔታ ፔንሲላቫኒያ ላይ የሴኔት መቀመጫን ያጡ ሲሆን ይሄን ለማካካስና አብላጫ መቀመጫ ለማግኘት፤ ኔቫዳና አሪዞና ዴሞክራቶች ያሸነፉ ሲሆን የጆርጂያ የሴኔት መቀመጫም ዴሞክራቶች ሰፊ የማሸነፍ ዕድል እንዳላቸው ተገምቶ ነበር።

በርካታ የሕዝብ አስተያየት አጥኚዎችና ታዋቂ ሚዲያዎች ሪፐብሊካኖች የተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫዎችን ያሸንፋሉ ብለው ቢተነብዩም አልሰመረም። በ2020 ምርጫ በርካታ የምክር ቤት መቀመጫዎችን ማሸነፋቸው በዚህ የዘመን አጋማሽ ምርጫ በቀላሉ ሊያሸንፉ ይችላሉ የሚል ትንበያ ነበር። ፍሎሪዳ ሪፐብሊካኑን ሮን ዲሳንቲስ ዳግም መረጠች።

ከ4 አመት በፊት የዴሞክራቱን አንድሪው ጂሉም ያሸነፉት በጠባብ ልዩነት ሲሆን፤ ዘንድሮ ግን በሰፊ ልዩነት በሁለት አኀዝ ማሸነፋቸው የ2024 ፕሬዝዳንታዊ እጩ ለመሆን ያግዛቸዋል እየተባለ ነው። የቀድሞው ፕሬዝዳንት ትራምፕ በዚህ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ተፎካካሪ ባይሆንም ተጽዕኖቸው ግን ቀላል አልነበረም። በዚያው ሰሞን ማራላጎ በሚገኘው የመኖሪያ ቤታቸው በሰጡት መግለጫ የደገፏቸው እጩዎች በአብላጫ ማሸነፋቸውን ገልጸዋል።

መሬት ላይ ያለው ሀቅ ግን ለየቅል ነው ይለናል ቢቢሲ፤ ትራምፕ ድጋፋቸውን ገልጸውላቸው የነበሩት አብዛኛዎቹ እጩዎች አልቀናቸውም። ፕሬዝዳንት ትራምፕ ከመደገፍ አልፈው እንዲመረጡ ይቀሰቅሱላቸው የነበሩት የፔንሲልቫኒያ ሴናተር ሜህሜት ኦዝ ሲረቱ፤ እንዲሁም ትራምፕ የደገፉቸው የጆርጂያው ሔርሼል ወከር 50 በመቶ ማሸነፍ ባለመቻላቸው 2ኛ ዙር ለመወዳደር ተገደው በመጨረሻ ተሸንፈዋል።

ትራምፕ ደግፈዋቸው የነበሩት ሌላው እጩ የአሪዞናው ብሌክ ማስተርስ ፤ በዴሞክራቱ ተቀናቃኛቸው እንዲሁ ተረተዋል። ሆኖም ሪፐብሊካኖች አሁንም ሴኔቱን የማሸነፍ ሰፊ እድል አላቸው ቢባልም መራጮች የተጠበቀውን ያህል ወጥተው ድምጽ ባለመስጠታቸው ጉድ ተሰርተዋል። ዲሞክራቷ የካንሳስ ገዢ ላውራ ኬሊ፤ የሪፐብሊካኑን እጩ ዴሪክ ሼሚት በመርታት ለ2ኛ ጊዜ ተመርጣለች።

አልጀዚራ አናገርኋቸው ያለው የቀድሞ ዴሞክራት ሴናተር፤ ጽንስ ማቋረጥን ተቃውመው መቆማቸው ሪፐብሊካኖችን ዋጋ አስከፍሏቸዋል ይላሉ። ሌላው ሪፐብሊካኖች እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ግሽበት ለምርጫ መቀስቀሻነት ሊጠቀሙበት ሲገባ ትኩረት አለመስጠታቸው ዋጋ አስከፍሏቸዋል ሲሉ ይደመጣሉ። በወግ አጥባቂ የሪፐብሊካን ተሿሚ ዳኞች ተጽዕኖ ስር የወደቀው የሀገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጽንስ ማቋረጥን ማገዱ በርካቶች ዴሞክራቶችን ለመምረጥ አነሳስቷቸዋል ይለናል ቢቢሲ። የፕሬዝዳንት ትራምፕን ድጋፍ ያገኙት አብዛኛዎቹ የሪፐብሊካን እጩዎች የድል በለስ ባይቀናቸውም የዊስኮንሰኑ ሴናተር ሮን ጆንሰን መቀመጫቸውን አስጠብቀዋል።

ብዙዎች ሚዲያዎችና የሕዝብ አስተያየት አሰባሳቢዎች እንደተነበዩት ሪፐብሊካኖች በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ቢያገኙም፤ ልዩነቱ በጣት የሚቆጠር ነው የሚሆነው እንዳሉት የሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሮቢንሰን ውድዋርድ ፤ በየአጋማሽ ዘመን ምርጫዎች ኋይትወስን የተቆጣጠረው ፓርቲ 31 መቀመጫዎችን ማጣት የተለመደ ነው ይላሉ ፕሮፌሰሩ፤ ቢል ክሊንተን 54፣ ባራክ ኦባማ 64፣ ዶናልድ ትራምፕ 38 መቀመጫዎችን በአጋማሽ ዘመን ምርጫ ቢያጡም ባይደን ግን በታሪክ አነስተኛ መቀመጫዎችን ነው የተነጠቁት።

የሮይተርሱ ጄሰን ላንጂ የአሜሪካ የአጋማሽ ዘመን ምርጫ ውጤትን ለማወቅ ቀናትንና ሳምንታትን መጠበቅ ግድ ነው እንዳለው ከብዙ ጥበቃ በኋላ ዴሞክራቶች አሸንፈዋል። በዚህ ምርጫ ተፎካካሪዎች ለ435 የኮንግረስ መቀመጫዎች ፣ ለ35 የሴኔት መቀመጫዎችና ለ36 ግዛቶች ተፋጠው ነበር። ሪፐብሊካኖች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በኮንግረሱ አብላጫ ድምጽ ለማግኘት አምስት ተጨማሪ መቀመጫዎችን ማግኘት የነበረባቸው ቢሆንም ከዚያ በላይ አሳክተዋል። ሴኔቱን ለመቆጣጠር ደግሞ ዴሞክራቶች አንድ መቀመጫ ማሸነፍ ይጠበቅባቸው የነበር ቢሆንም ከጆርጅያው ጋር ሁለት መቀመጫዎችን በመርታት ሴኔቱን በእጃቸው አስገብተዋል።

ስለ አሜሪካ ምርጫ የምንፈተፍተው ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በአዎንታ ወይም በአሉታ በሀገራችን ላይ ተጽዕኖ ስላለው ነውና አንዳንድ ነጥቦችን እናንሳ። አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከጀመረች ወደ 120 አመታት እየተጠጋት ነው። በአሜሪካም ሆነ በኢትዮጵያ መንግስታት ቢቀያየሩ አንድ ጊዜ ሞቅ ሌላ ጊዜ ቀዝቀዝ አልፎ አልፎም ለብ እያለ ቀጥሏል።

የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት አሜሪካ ከሌሎች ሀገራት ጋር ታራምደው ከነበረ ግንኙነት የተለየ አልነበረም። ከብሔራዊ ጥቅሟ በተጻራሪ የሚቆም መንግስት በመጣ ጊዜ ለመቀየር የማትፈነቅለው ድንጋይ የለም። በ19ኛው መክዘ እኩሌታ ማብቂያ አካባቢ በላቲን አሜሪካ በደቡብ ምዕራብ ፓሲፊክ እንዲሁም በ20ኛው መክዘ መግቢያ ደግሞ፤ በፓናማ ፣ ሆንዱራንስ ፣ ኒካሯጓ ሜክሲኮ፣ ሄይቲና ዶሚኒካን ሪፐብሊክ መንግስታትን ለውጣለች።

በተለይ በቀዝቃዛው ጦርነት (1945-1991 እኤአ) ዓለም በሶሻሊስትና በካፒታሊዝም ርዕዮተ ዓለም ጎራ በተከፈለ ጊዜ የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነት ሻክሮ ነበር። ደርግ ሶሻሊስት ስለነበርና አሰላለፉም በሶቭየት ሕብረት ረድፍ ስለነበር አሜሪካና አጋሮቿ ለተቃዋሚዎች በግልጽ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ በማድረግ፤ ደርግን በተራዘመ ትጥቅ ትግል ገርስሰው አስመራንና አዲስ አበባ እንዲገቡና የስልጣን መንበሩን እንዲቆጣጠሩ በማድረግ የማይተካ ሚና ተጫውተዋል። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ አሜሪካ ባለፉት ሁለት አመታት የኢትዮጵያን መንግስት የመቀየር ያልተሳካ ሙከራ አድርጋለች።

በተለይ አሜሪካ በኢትዮጵያ እንዳደረገችው በመላው ዓለም የ70 ሀገራትን መንግስት ለመለወጥ በህቡዕና በይፋ ተንቀሳቀሳለች። የቀዝቃዛው ጦርነት በበርሊን ግብ መፍረስ በሶቪየት ሕብረት መበታተን ከተቋጨ ከ30 አመታት በኋላ፤ ዛሬም የማትፈልገውን መሪ ለማስወገድ በምርጫ ጣልቃ ትገባለች በውክልና ወይም በቀጥታ መንግስት ትገለብጣለች።

ሀገሬን ያለ ብሔርተኛ/nationalist/ ተላላኪና አሻንጉሊት አልሆንም ያለና ለዜጋው ጥቅም የቆመ መንግስት፤ ከአሜሪካና ከምዕራባውያን ጥቅም በተጻጻሪ እንደቆመ እንደጠላት ተቆጥሮ እንዲወገድ ይደረጋል። ባላንጣየ ከምትላት ቻይና ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለውም በጠላትነት ተፈርጆ ጥርስ ይነከስበታል። የቡርኪናፋሶው ቶማስ ሳንካራ የጋናው ኩዋሚ ንኩሩማህ የኢራቁ ሳዳም ሁሴንና የሊቢያው ሞአመር ጋዳፊ ከሰለባዎቿ መካከል ይጠቀሳሉ።

በምርጫ ጣልቃ መግባትም ሆነ የመንግስት ለውጥ ማምጣት የአሜሪካንን ጥቅም ለማስከበር አዋጭ ነው ቢባልም፤ መጨረሻው ግን ሀገራትን ወደለየለት የእርስ በርስ ጦርነት እና ቀውስ ስለሚዘፍቅ ውጤታማ ባይሆንም ዛሬም በጀ ብላ ቀጥላበታለች። የቅርቦቹን እነ አፍጋኒስታን፣ ኢራቅ ፣ ሶሪያ ፣ የመን ፣ ቬኒዞላንና ሄይቲ ልብ ይሏል።

ዛሬም ጥቅሜን ያስከብርለኛል የምትለውን መንግስት ለማንገስ በኢራንና በሶሪያ በሌሎች በርካታ ሀገራት አሻንጉሊትና ተላላኪ መንግስት ለመተካት ሌት ተቀን እያሴረች ነው። አሜሪካ እኤአ 1946-2000 በ81 ሉዓላዊ ሀገራት ምርጫ በይፋ ወይም በስውር ጣልቃ ገብታለች። በጣሊያን፤ በፊሊፒንስ፣ በሊባኖስና በጃፓን ምርጫዎች ጣልቃ በመግባት እንዳሻት የምታሽከረክረው መንግስት እንዲመረጥ አድርጋለች።

የመንግስታቱ ድርጅት ቻርተር አንቀጽ 2 ቁጥር 4 ላይ በግልጽ የአንድን ሉዓላዊ ሀገር መንግስት፤ በኃይልም ሆነ በሴራ ለመለወጥ የሚደረግ እንቅስቃሴን የሚያወግዝ ድንጋጌ ከጸደቀ በኋላ እንኳ አሜሪካ ይህን አለማቀፍ ሕግ በመተላለፍ የ70 ሀገራትን መንግስታት ለውጣለች። ለዓለም ሰላም ለሕግ ልዕልና ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ቆሜያለሁ የምትለው አሜሪካ እንዲህ ናት።

ቆሜለታለሁ የምትለው እሴትና መርህ የውሸት ነው። ስለዚህ ከአሜሪካ ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በጥንቃቄ ማየትና መከታተል ያሻል። ከሁሉም በላይ አሜሪካንን ለጣልቃ ገብነት የሚጋብዙ ቀዳዳዎችን እየተከታተሉ መድፈን ልዩ ትኩረት ይሻል። ውስጣዊ አንድነት ላይ ያልሰራናቸውን ተግባራትም በጊዜ መከወን ይጠይቃል።

ዘላቂው መፍትሔ ምዕራባውያን ድህነታችንና ኋላቀርነታችንን መያዣ አድርገው ዝቅ አድርገው እንዳያዩን ፤ ከፍ ሲልም በእርዳታና በብድር ሰበብ በነጻነታችንና በሉዓላዊነታችን ላይ እንድንደራደር እጃችን ለመጠምዘዝ የሚደረገውን ጥረትና ጫና ለመቋቋም የድህነትንና የኋላቀርነትን ቀንበር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መስበር አለብን። የግብርናውን፣ የኢንዱስትሪው፣ የአገልግሎት ዘርፉን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የድህነትንና የኋላቀርነትን ቀለበት ሰብረን የመውጣት ጉዳይ ለነገ የሚተው ጉዳይ አይደለም።

አስተማማኝ የስራ ዕድል መፍጠር ፤ የዋጋ ግሽበትንና የኑሮ ውድነትን ከመቀነስ ጎን ለጎን ደግሞ የዴሞክራሲ፣ የደህንነትና የጸጥታ ተቋማትን መገንባ ፤ የሕዝብን አንድነት የሚሸረሽሩ ፖለቲካዊ ሴራዎችንና ደባዎችን ተቆራርጦ መታገል ፤ ብልሹ አሰራሮችንና ሙስናን ፤ ጽንፍ የረገጠ ብሔርተኝነትን ፤ ወዘተረፈ ማስወገድ ፤ ውስጣዊ ለቀውስ ተጋላጭነትን ከመቀነስ ባሻገር እንዳለፉት ሶስትና አራት አመታት ያሉ ያላባሩ ጫናዎችን ለመመከት ጉልበት ይሆናሉ።

ከውጭው ጫና ይልቅ እነዚህን የቤት ስራዎቻችንን አበክረን ባለመከወናችንና ባለመስራታችን የሚመጣብን አደጋ የከፋ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ይበል የሚያሰኙ ናቸው። መንግስት ምንም እንኳ ወደ ስልጣን ከመጣበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ በየአቅጣጫው ዘርፈ ብዙ የጥቃት ግንባሮች ተከፍቶበት ፋታ ባያገኝም ተስፋ የሚጣልባቸውን ተግባራት አከናውኗል።

ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን በአፋር ክልል እየለማ ያለ የጥጥ እርሻን በጎበኙበት ወቅት ፤ " አባቶቻችን ደማቸውን አፍስሰው ፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ያጎናጸፉንን ሉዓላዊነትና ነጻነት በላባችን ማስከበር ካልቻልን ልናጣው እንችላለን። " በማለት ድህና ተመጽዋች ሀገር ነጻና ሉዓላዊ ሊሆን እንደማይችል አጽንኦት ሰጥተዋል።

አመቱን ሙሉ የሚገማሸሩ ወንዞችን ፣ ሊታረስ የሚችል ሰፊ ለም መሬትንና አምራች የሰው ኃይሉን አቀናጅተን በአመት ሁለትና ሶስት ጊዜ በማምረት በምግብ እህል ራሳችንን ችለን ለፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚተርፍና ለውጭ ገበያ የሚቀርብ አምርተን ከድህነትና ከኋላቀርነት ካልተላቀቅን አያት ቅድመ አያቶቻችን መስዋዕት ሆነው ያቆዩን ነጻነትና ሉዓላዊነት ሙሉ ሊሆን አይችልም፡፡

ለዚህ ነው የለውጥ ኃይሉም ሆነ የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ መንግስት ወደ ኃላፊነት እንደመጣ ድፍረት የተስተዋለባቸውን ማሻሻያዎችን ያደረገው በተለይ የሕዳሴው ግድብ ላይ ተደቅኖበት የነበረን አደጋ የመቀልበስ ፤ የአረንጓዴ አሻራ ፣ የኩታ ገጠም እርሻ፣ የበጋ ስንዴ ፣ የሜካናይዜሽን ግብርናን ፣ ወዘተረፈ በመተግበር የሚጨበጥ ለውጥ ያመጣው። ሕዳሴውን ከለየለት ክሽፈት ታድጎ ለዚህ ስኬት የበቃው።

ካለፈው አመት ጀምሮ ስንዴን ከውጭ ማስገባት አቁሞ ራሱን የቻለው ፤ በዚህ አመት ደግሞ ወደ ውጭ ለመላክ ያቀደው። ይህ ስኬት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን አካልና መደላድል ነው። ውስጣዊ ድሎቻችን ለውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን አቅም ናቸው። ከፍ ብዬ የጠቀስኋቸው ሶስቱ ኩነቶች ወደዚህ የሚያደርሱ ናቸው። አንድ ምስል ይከስታሉ ያልሁትም ይሄን ነው።

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጉምቱ አሜሪካዊ ሪቻርድ ሀስ ፤ " የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከሀገር ቤት ይጀምራል ፤ "/ FOREIGN POLICY BEGINS AT HOME :..." በሚል መጽሐፉ ይሄን ይተነትናል። ጠቅላይ ሚንስትሩና መንግስታቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከሀገር ውስጥ እንደሚጀምር አበክረው ተገንዝበው እየሰሩ ያሉት ለዚህ ነው።

**የሀገራችንን ሰላም ፈጣሪ ያጽናልን !**
**ሻሎም !**
**አሜን ።**

# የሕይወት ገጽታ

# "ሱስ ትልቅ የሀገር ችግር፤ የትውልድም መጥፊያ ነው"

**- ሲስተር ይርገዱ ሀብቱ**

**አዲስ ሕይወት የእፅና አልኮል ሱሰኝነት ህክምናና ማገገሚያ ማዕከል መስራች**



ፎቶ ፡- በገባቦ ገብሬ

**እፀገነት አክሊሉ**

ሲስተር ይርገዱ ሀብቱ ለቤተሰባቸው ሶስተኛ ልጅ ሲሆኑ፤ ከሆለታ ከተማ በ7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ ገጠር ውስጥ ነው የተወለዱት። ከአርሶ አደር ቤተሰቦቻቸው ጋር በጥሩ ፍቅርና ስነ ምግባር አድገዋልም። ኋላም እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አያቶቻቸው ለአካባቢው ነዋሪዎች ባስገነቡት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸው እንዲጀምሩ ሆነዋል። እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርታቸውን በዚሁ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።

"... የድሮ ቤተሰብ እንደ አሁኑ አይደለም፤ አንዳንዶች ጭራሽ ትምህርት ለማስተማርም ላያስቡ ይችላሉ። ግን ደግሞ ትምህርት ማስተማር አለብን ብለው የሚነሱት እንደእኔ አይነት ቤተሰቦችም ቢሆኑ ስለትምህርት ጥቅም ጠለቅ ያለ እውቀት አይኖራቸውም። ይህ ደግሞ የልጃቸውን እጅ ይዘው ትምህርት ቤት አስገብተው ከመመለስ ውጪ የሚያደርጉት ነገር እንዳይኖር ያደርጋቸዋል። እኔም በወቅቱ ወላጆቼ እጄን ይዘው ትምህርት ቤት አስገቡኝ እንጂ ከዚያ ባለፈ ያደረጉልኝ ምንም ነገር አልነበረምና ሙሉ በሙሉ የራሴው ጥረት ነበር የሚንጸባረቀው" በማለት የትምህርት ጅማሯቸውን ያስታውሳሉ።

ሲስተር ይርገዱ በዚህ መልኩ የተቀላቀሉትን የትምህርት ዓለም በጣም የተመቻቸ ባይሆንላቸውም ብዙ አላስከፋቸውም። ትምህርትም ይወዱ ስለነበር ችግሮቹን ሁሉ እየተጋፈጡ ማለፍ ችለው ነበር። ምክንያቱም በአያቶቻቸው ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለውን የትምህርት ሂደታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ ሰባተኛ ክፍል ላይ ሌላ የትምህርት ዓለምን ነው የተቀላቀሉት። ሌላ የሕይወት ገጽታን ያዩበትም ሆኖ ነው ያለፈው። ያንን ሲያስታውሱም እንዲህ ነበር ያሉት ‹‹...ሰባተኛ ክፍል ከገባሁ በኋላ ትምህርት ቤቱ ከመንደራችን የሰባት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ነበረውና በቀን ውስጥ ስሄድ ስመጣ 14 ኪሎ ሜትር በእግር እጓዝ ነበር። በጉዞው ተሰላችቼ ትምህርቴን አላቋረጥኩም። ይልቁንም ከጓደኞቼ ጋር ቀጠልኩት" ይላሉ።

እሳቸውና መሰሎቻቸው ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በእግራቸው አቋርጠው መሄዳቸው ነገን ለማሳመር መሆኑ በእጅጉ ገብቷቸዋል። በዚህም ምንም ዓይነት ቅሬታ አይሰማቸውም። የሚገርመው ነገር ደግሞ ያንን ሁሉ ኪሎ ሜትር አቋርጠው ሄደው ተምረው ሲመለሱ ቤት የሴቶች ሥራ ይጠብቃቸዋል። በዚህም ተቃውሞ የላቸውም። ቤተሰቦቻቸው ስለ ትምህርት እምብዛው ግንዛቤው አልነበራቸውምና ማታ ኩራዝ አብርቶ ጋዝ እየጨረሱ ማጥናት አይፈቀድም። ይህም ቢሆን አንድም ቀን ተስፋ አያስቆርጣቸውም። ይልቁንም ሲስተርና ጓደኞቻቸው ትምህርታቸውን የሚያጠኑበትን፣ የቤት ሥራቸውን የሚሰሩበትን መላ ዘየዱ እንጂ።

"...እንደ ነገርኩሽ የእኔም ሆኑ የሌሎች ጓደኞቼ ወላጆች ስለ ትምህርት የነበራቸው ግንዛቤ ውስን በመሆኑ ልጅን ትምህርት ቤት ከመላክ ባለፈ የሚያግዙት ነገር አልነበረም። እንደውም ጋዝ አትጨርሱ በሚል ማታ ኩራዝ አብርቶ ሁሉ ማጥናት አይፈቀድም። ነገር ግን እኔና ጓደኞቼ ያንን ሁሉ ኪሎ ሜትር በእግራችን አቋርጠን ስንመጣ ምንም ዓይነት ከትምህርት ውጭ የሆነ ወሬ አናወራም፤ የተማርነውን እንጠያየቃለን ቆም እያልን የቤት ሥራችንን እንጨርሳለን፤ እንዲህ እንዲህ እያልን ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም ነበር የምንማረው" ይላሉ።

በራሳቸው ጥረት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን የወሰዱት ሲስተር ይርገዱ፤ የትምህርት ውጤታቸው የነርስነት ሙያን ለመማር የሚያበቃ ነበርና በ1972 ዓ.ም በቀጥታ ወደ ነርሲንግ ትምህርት ቤት አመሩ። ምንም እንኳን ነርስ የመሆን ፍላጎት ባይኖራቸውም አንድ የትምህርት መስክን መርጦ ሥራ የመግባት ፍላጎቱ ስለነበራቸው ትምህርቱን መከታተል ጀመሩ።

"...ወደ ነርስነት ሙያ የገባሁት ተምሬ ሥራ ለመያዝ ካለኝ ፍላጎት እንጂ የልጅነት ህልሜ ሆኖ አልነበረም፤ ነገር ግን ከገባሁበት በኋላ በጣም ወደድኩት፤ ትምህርቱም ላይ ሆኜ ታካሚዎች በህመም ሲሰቃዩ ሳይ፤ በምንኖርበት አካባቢም እናት የእንግዴ ልጇ ለይቶ የሚያወጣላት አጥታ ሕይወቷን ስታጣ ያየሁትና የሰማሁት ነገር ሁሉ ፊቴ ይመጣ ጀመር። ከዚያ በኋላ እንደውም ከመውደድም አልፌ ምነው ቀደም ብዬ ነርስ ሆኜ በነበረ እረዳቸው ነበር ሁሉ ብዬ መቆጨት ጀመርኩ። በዚህም ከእለት እለት ፍላጎቴ እየጨመረ ሄደ" በማለት ሁኔታውን ይገልጹታል።

የነርስነት ትምህርታቸውን በወለጋ ነቀምት ነርስ ትምህርት ቤት የተከታተሉት ሲስተር ይርገዱ፤ በተለይም የመጀመሪያዎቹን ስድስት ወራት አካባቢን ለመልመድ ብሎም ከትምህርቱ ጋር እስኪዋሃዱ ድረስ ከፍ ያለ ጊዜን ወስዶባቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። እንዲያውም አስጨንቋቸው እንደነበር አይረሱትም። ‹‹...እንግዲህ ትምህርት በገጠር በራስ ጥረት የሚታለፍ ነው ፤ ቤተሰብም ልጆቹን ትምህርት ቤት ላክሁ ከማለት ውጭ የሚወረውረው ጠጠር የለም። እንደውም ልጆች ከትምህርት ሲመለሱ የቤቱን ሥራ እንዲያግዙ ይፈልጋሉና ምንም እንዲያጠኑ አይፈቅዱላቸውም። ስለዚህም በዚህ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሄደን ነው 12ተኛ ክፍልን ማጠናቀቅ የቻልነው። ጠንክረን ያለንን አቅም ሁሉ አሟጠን ብንጠቀም የት እንደርሳለን የሚለውን አላሰብነውም፤ ይህንን እንድናስብ እድል የሚሰጠን የለም። እናም ከፍ ወዳለ የትምህርት ደረጃ ስንገባ ሁሉም ነገር ከባድ አስጨናቂ ይሆናል። እኔም ላይ የደረሰው ይኸው ነው" ይላሉ።

ነርስ ትምህርት ቤት ገብተው መማር እንደገና የሆነባቸው ሲስተር ይጋርዱ፤ የሚችሉትን እየሞከሩ የከበዳቸውን ከመምህራኖቻቸው በተለይም ከጓደኞቻቸው ጋር ሰፊ ጊዜ ሰጥተው እያጠኑ ብዙ ተጉዘዋል። ሆኖም ከቤት ወጥተው አለማወቃቸውና የቤተሰብ ናፍቆት እንዲሁም አንዳንድ ፈታኝ ሁኔታዎች ሲደረስባቸው ግን ‹‹በቃ ይቅርብኝና ትቼ አገሬ ልግባ›› ብለው በተደጋጋሚ ተመኝተዋል። ይህንን ሲያስታውሱም "...በሁለት ልብ ውስጥ ብሆንም ጠንክሮ መስራት ግን የማያሻግረው ዳገት እንደሌለ ተረዳሁ። እንዳልኩሽ ትምህርትን የሙሉ ጊዜ ስራዬ በማድረጌ ከስድስት ወራት በኋላ ሁሉም ነገር ገብቶኝ ጎበዝ ተማሪ የምባል ሆንኩኝ" በማለት የነርስ ትምህርት ቤት ቆይታቸውን እንዲሁም ሰው ለሚማረው አልያም ለሚሰራው ሥራ ጊዜን መስጠት ከቻለ ያሰበበት የማይደርስበት ምክንያት እንደሌለ ማየታቸውን ይናገራሉ።

የነቀምት ነርስ ትምህርት ቤት ቆይታቸውን ሲያጠናቅቁ የተመደቡት በአዲስ አበባ አቃቂ ጤና ጣቢያ ሲሆን፤ ህበረተሰቡን በትጋት እያገለገሉ ሶስት ዓመት ከስድስት ወር አካባቢ የሰሩበት ነው። በወቅቱ በተመደቡበት ጤና ጣቢያ ሀኪም እንደልብ ስለማይገኝ የሀኪሞቹን ቦታ ሸፍነው ይሰሩ ነበርም። ይህ ደግሞ ለሥራው እንዲጨነቁ ሁሌ ሲነጋ አዲስ እውቀት እንዲይዙ አድርጓቸዋል። በሥራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት በጣም አንባቢ መሆን እንዳለባቸውም ያስገነዘባቸው ነው።

በሽተኛን ችግሩን ለይቶ ለማወቅ ለዛ ሊሆን የሚችል መድሃኒት ለማዘዝ የግድ ንባብ ያስፈልጋል። ያንን ደግሞ ሁሌም በስኬታማነት ለማጠናቀቅ ይጥሩ ነበር፤ አድርገውታልም። ይህ ደግሞ የነበራቸውን እውቀት ከፍ ከማድረጉ ባሻገር ለሥራው ያላቸውን ፍላጎት በሚገባ እንዲወጡበት አግዟቸዋል። ይህ የሥራ ትጋታቸው እንዲሁም ለሙያው ያላቸው ፍላጎት በአለቆቻቸው ዓይን ጥሩ ግምት አሰጥቷቸውም ወዲያው በ1978 ዓ.ም ወደ ጳውሎስ ሆስፒታል ተዘዋወሩ። ጳውሎስ ሆስፒታልም ለ35 ዓመት ያህል አገለገሉ።

እሳቸው ይሰሩበት ከነበረበት ጤና ጣቢያ ጳውሎስ ሆስፒታል በአሰራሩም ሆነ በስፋቱ የተለየ ነው። ሲስተር ይርገዱ ግን እዛም ቢሆን በትጋት ነበር የሚያገለግሉት። ማንንም ሳይጠብቁ መሥራት ያለባቸውን ነገር ያደርጋሉ። ሆኖም አንዳንድ አስገዳጅ ሁኔታዎች ግን ያጋጥሟቸዋል። ይህም የቀደመውን የአሰራር ባህላቸውን መከተል አይችሉም። ምክያቱም ይህ ብዛት ያለው ሰው የሚስተናገድበትና ሁሉም በተሰጠው ኃላፊነት ልክ የሚጓዝበት ነው። አካሄድና አሰራሩ የተለየ ነው። ስለዚህም አሰራርን ወይንም ደግሞ ተዋረድን ጠብቀው መስራት ግዴታቸው ነው።

‹‹...ጳውሎስ ሆስፒታል ሥራ ሲጀምር የተመደብኩት ሚሊተር ዋርድ የሚባል ክፍል ነበር። እዛ ሆኜ አንድ ሰው መጣና ህክምና ጠየቀኝ። ትኩሳቱን ለካሁ፣ ደም ምርመራ ላኩት የላብራቶሪ ውጤቱ ሲመጣም ሰውዬው የወባ በሽታ ተገኘበት። ይህንን ተመልክቼም ራሴ መድሃኒት አዘዝኩለት። በዚህ ተግባሬ ደግሞ በማግስቱ ተከሰስኩ። ተከስሼ የቀረብኩባት ኃላፊም በትህትና ተቀብላኝ ቀድሞ የነበርኩበትና አሁኑ ያለሁበት ሁኔታ የተለያየ የሥራ ቅደም ተከተል እንዳለው፤ ሀኪሞች በብዛት ስላሉም እነሱም ሥራቸውን እንደሚሰሩ በመናገር እኔም በሀኪሞቹ ስር ሆኜ ሥራዬን ማከናወን እንዳለብኝ ነገረችኝ" በማለት ጳውሎስ ሆስፒታል ሥራ ሲጀምሩ ያጋጠማቸውን ያብራራሉ።

በዚህ ሁኔታ ሥራቸውን እየሰሩ በሆስፒታሉ አሉ የተባሉ ሀኪም ሆነው የቀጠሉት ሲስተር ይርገዱ፤ በተከታታይ ታታሪና ምስጉን ተብለው ተሸልመዋል። ልክ በ50 ዓመት እድሜያቸውም በዲፕሎማ ቀርቶ የነበረውን ትምህርታቸውን እንደገና በመጀመር ወደ ዲግሪ ደረጃ ከፍ አድርገዋል። ይህንን ደረጃ ከያዙ በኋላ ሌላኛውን ኃላፊነት ወደመሸከሙ ገቡ። ይህም የቤተሰብ ኃላፊነት ሲሆን፤ ወደ ትዳር ገብተው የራሳቸውን ቤተሰብ ማቆም ጀመሩ።

## የትዳር ምስረታ

ሲስተር ይርገዱ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ሥራው ዓለም የተቀላቀሉት በ1975 ዓ.ም ነው። በዚሁ ዓመትም ትዳር መስርተዋል። ዘንድሮም በትዳር 40 ዓመት ሆኗቸዋል። "...ትዳር ከባድ ነው ፤ ባልና ሚስት የሚሆኑት ሰዎች አብረው ከመሆናቸው በፊት ሁሉም በየፊናቸው ያደጉበት አስተሳሰብ፣ ባህል ፣ወግ የቤተሰብ ሁኔታና ሌላም ሌላም ነገር አለ። ትዳር ደግሞ እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች አስማምቶና አስታርቆ መሄድን የሚጠይቅ ተቋም ነው። እኛም እንደማገኘነው ባለትዳሮች እነዚህን ነገሮች አጣጥመን ትዳራችንን በጸና መሰረት ላይ ለማቆም ጊዜ ወስዶብናል።›› ይላሉ።

ይቀጥሉናም ‹‹እኔ ደግሞ እናትና አባቴ 65 ዓመታትን በትዳር ሲቆዩ እነሱ ላይ አይ የነበረው መደማመጥና መከባበርን ነበር። እኔ ጋር ስመጣ ደግሞ እንደው ትንሽ ነገር እንኳን ከተናገረኝ እንዴ አባቴ እናቴን እኮ ተናግሮ አያውቅም እልና እቆጣ ነበር ፤ ዞሮ ዞሮ ትዳር ቀላል አልነበረም ለማለት ነው። በሂደት ግን ይህ ነገር መስመሩን ይዟል። ባለቤቴ የእኔን ባህርይ ተረዳ እኔም የእርሱን አስተሳሰብ አወቅሁት። እናም በስተመጨረሻ ነገሮች እየተስተካከሉ ትዳራችን መስመር ያዘ። በዚህም አራት ወንድ ልጆችን ለመውለድ በቃን" በማለት ስለ 40 ዓመት ትዳራቸው አመሰራረት ይናገራሉ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

" ...የሆስፒታል ሥራ አይደለም ልጆች ወልዶ ለማሳደግ የቤተሰብ ኃላፊነት ብቻ ለመወጣት እንኳን በጣም ከባድ ነው። ነገር ግን ወቅቱ ጥሩ ስለነበር እናትን ተክተው የቤት ሥራ እየሰሩ ልጆችን የሚንከባከቡ ልጆች ነበሩበትና ችግሮች በመጠኑም ቢሆን አልፈዋል። እንደ እናት ሳየው ግን ልጆቼን ጥዬ ሆስፒታል ሳድር ጠዋት እኔ ስመጣ እነሱ ትምህርት ቤት ሲሄዱ የማንገናኝባቸው ጊዜያት ነበሩና ቅር እሰኝ ነበር። ሆኖም ሥራ ስለሆነ ምንም ማድረግ አልችልም። በዚያ ላይ ባለቤቴም ልጆቼም ይረዱኝና ያግዙኝ ነበርና ደስተኛ ሆኜ ጊዜውን አሳልፌዋለሁም " ይላሉ የሆስፒታል ሰራተኛ ሆኖ የቤተሰብ ኃላፊነት ሲደረብ ያለውን ፈተና ሲያስታውሱ።

ሲስተር ይርገዱ በሥራቸውም በቤተሰብ ሕይወታቸውም የተሳካላቸው ቢሆኑም በተለይም የመጨረሻው ልጃቸው ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለ የገጠመው የሱስ ችግር የሲስተር ይርገዱንና ቤተሰባቸውን የሕይወት ጉዞ ወደሌላ አቅጣጫ የመራው ነበር። ለአስር ዓመታት ያህል ልጃቸው እሳቸው እንዲሁም መላው ቤተሰቡ ሊያልፈው የተገደደው ችግር በቀላሉ የሚገለጽ አልነበረም። ይህም ቢሆን ግን ለሌሎች የተረፈ ሥራን እንዲሰሩ እድሉን ሰጥቷቸዋል። የብዙዎች ተስፋ መሆን የቻለም ነው። ብዙዎችን ከሞት ወደ ሕይወት የቀላቀለም ነበር። የብዙ ቤተሰቦችን እምባ ያበሰ።

"...አንዳንዶች ልጅሽ ችግር ውስጥ ባይገባ ኖሮ ለሌሎች ብርሃን የሆነውን ሥራ አትሰሪም ነበር ይሉኛል ፤ አዎ እኔም ሳስበው ሰው ሰላም ከሆነ ሆነ ነው እንዴትም ብዬ ልገባበት አልችልም ነበር፤ የሌላውንም ችግር አላይም ነበር እላለሁ። ሱስ የብዙ ሰዎች ሕይወት መመሰቃቀል፣ የትዳር መፍረስ፣ ወጣቶች እራሳቸውን የማጥፋት፣ ቤተሰብ የመበተን ምክንያት ነው።» ያሉን እንግዳችን፤ ጳውሎስ ሆስፒታል የስነ ልቦና አማካሪ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ ያጋጠማቸው ነገር ስለነበር ኋላም የራሳቸው ልጅ በችግሩ ውስጥ ገብቶ ሲመለከቱት ችግር ፈቺ ለመሆን እንዳሳሰባቸው ያስረዳሉ።

### አዲስ ሕይወት ለሱሰኞች

« አዲስ ሕይወት የእጽና አልኮል ሱሰኞች ማገገሚያ ማዕከልን የከፈትኩትና እዚህ ሥራ ውስጥ የገባሁት እንደነገርኩሽ የሱስን አስከፊነት ቤቴ ድረስ ገብቶ በኑሮዬ ላይ ታይቶ ስላስተማረኝ ነው። እኔ ፈጣሪ እንዲሁም ህክምና አግዞኝ ልጄ ከችግሩ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆን አድርጌያለሁ። ያቋረጠውን ትምህርት ቀጥሎ በማዕረግ ተመርቆ ኋላም ትዳር መስርቶ የልጆች አባት ሆኖም አይቼዋለሁ። ሌሎችስ ስል ግን መልስ የለኝም። በተለይ ያልተማሩት ምን እንደሚውጣቸው ሁሌ ያሳስበኛል። ስለዚህም ከእኔ ውጭ ያስተማረው የለምና ለሌላ መትረፍ እንዳለብኝ ወሰንኩኝ። ወደስራው ስገባ ግን ምንም ነገር አልነበረኝም፤ ለራሴ የምኖርበት ቤት የምንቀሳቀስበት መኪና እንኳን የለኝም። ነገር ግን እኔም ሆንኩ ልጄ እንዲሁም መላው ቤተሰቤ ስናስበው በሱስ ምክንያት የብዙ ኢትዮጵያውያን ቤት ታምሷል፤ ብዙ ወጣቶች መስራትና መለወጥ አልቻሉም። ሀገራቸውን ማገዝ ባለባቸው ልክም ማገዝ ተስኗቸዋል። ራሳቸውን ቤተሰባቸውን እንዲሁም ሀገራቸውን መጥቀም በሚችሉበት እድሜ ላይ ቢሆኑም ለከፋ ችግር ተጋልጠው ቁጭ ብለዋል። ስለዚህም በልጄ ሀሳብና ፍላጎት በቤተሰቤ ተሞክሮ መነሻነት ሥራውን አሀዱ አልነው» ይላሉ ስለ ማዕከሉ አመሰራረት ሲናገሩ።

"...ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ለሰራኋቸው 35 ዓመታት አርአያ የምትሆን ነርስ በሚል ሆስፒታሉ አምስት ሺህ ብር እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስድስት ሺህ ብርና ሜዳሊያ በሽልማት አበርክተውልኝ ነበር። ይህ ለእኔ በተለይም ላሰብኩት ሥራ መነሻ የሚሆነኝ ብዙ ብር ነበር። ከዚያም ደግሞ አንዳንድ ሃሳቡን የወደዱት ቤተሰቦቼ የአቅማቸውን አገዙኝ። በዚህ ሁኔታ ሄድኩና አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ አጠናቀቅሁ። ትልቅ ገንዘብ የሚፈልገውን የቤት ኪራይ ግን በቀላሉ የምሸፍነው አልሆነልኝም። በዚህም የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ስራ አስኪያጅ በጣም



መልካም ስለነበር ጉዳዩን ሳማክረው ችግሩን ተረድቶ አንቺ ልክ በጎ ሀሳብ ካሰበች እኛም አብረንሽ ልንሰራ ዝግጁ ነን አለኝ። ሌሎች ኃላፊዎችን አስተባብሮም ሆስፒታሉ አጋር ሊሆን ቃል ገባ። በዚህም እነሱ የቤት ኪራዩን እየከፈሉ ባለሙያና ምግብ እያቀረበልኝ እንድሰራው ሆንኩ» ይላሉ የማዕከሉ ጉዞ በምን መልኩ እንደቀጠለ ሲያስረዱ።

ማዕከሉ ባዘጋጃቸው 12 አልጋዎች ላይ ከሱስ ለማገገም ጥረት የሚያደርጉ ወጣቶች አሉ። እነዚህ ወጣቶች ደግሞ ለሶስት ዓመታት ያህል በነጻ ሲገለገሉ ቢቆዩም ነገር ግን ጳውሎስ ሆስፒታል ይከፍል የነበረውን ቤት ኪራይ ሲያቋርጥ ሁሉም ነገር ተደራረበ። ደመወዝ፣ ውሃና መብራት እንኳን መክፈል ሲያቅት ከተገልጋዮቹ ጋር ወጪ መጋራት ወይንም ደግሞ የአገልግሎት ክፍያ በማለት አንድ ሰው በወር 6ሺህ 219 ብር እንዲከፈል ሆኗል የሚሉት ሲስተር ፤ ይህም ሆኖ ከ12ቱ አልጋ ሁለቱ ምንም ዓይነት ገቢም ሆነ ደጋፊ ለሌላቸው ወገኖች በነጻ አገልግሎት የሚሰጥበት መሆኑን ይናገራሉ። ጳውሎስ ሆስፒታል ግን እስከ አሁን ድረስ በሳምንት ሁለት ቀን ሀኪሞች፣ ሳይኮሎጂስቶች እየላከ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገላቸው እንደሚገኝ አልሸሸጉም።

### ትኩረት ለልጆች አስተዳደግ

ልጆችን ጥሩ ማብላት፣ ማጠጣት፣ ማዝናናት፣ ጥሩ ትምህርት ቤት ማስተማር መልካምና የሚበረታታ ወላጅም ለልጁ ሊያደርግ የሚገባው ነገር ነው። እኔም የሚመስለኝ ይኸው ነበር። ነገር ግን ልጅ ማሳደግ ይህ ብቻ አይደለም። እኔ ድሮ ስማር ትኩረት አለማግኘቴን ለማጥናት እንኳን የተመቻቸ ሁኔታ አለመኖሩን እያስታወስኩ ያንን ለመበቀል ነበር ልጄን ከፍዬ ሳስተምር የነበረው። ግን ያ ብቻ በቂ እንዳልሆነ አውቄያለሁ። ምክንያቱም ልጆች ከዚያም ያለፈ እንክብካቤን ይፈልጋሉ።

በሌላ በኩል ዛሬ ላይ ያሉ ልጆች እንክብካቤው ስለሚበዛባቸው ሁሉም ነገር በእጃቸው ስለሆነ ለአቻ ግፊትም ሆነ በራሳቸው ለሚያደርጉት ነገር ቅርብ ናቸው። ይህ ደግሞ ገና በዘጠኝና አስር ዓመታቸው ሱስ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። በመሆኑም እኛ ፍላጎታቸውን ማሟላት ብቻ ሳይሆን ባህሪያቸው ላይ መስራት አለብን ይላሉ። ለምሳሌ፡- ልጆች የመጀመሪያ ባህሪያቸውን የሚወስዱት ከየትም ሳይሆን ከቤተሰባቸው ነው። የሚቀጥለውን ከአካባቢያቸው ይማራሉ። በመሆኑም በተቻለ መጠን ሰዎች ልጆች ከወለዱ በኋላ ለልጆቻቸው ጊዜ መስጠት፤ ባልና ሚስት ራሳቸው የግላቸው ጊዜ ማዘጋጀት፤ በልጆች ዙሪያ ሁልጊዜ መነጋገር አለባቸው። ስልኩን፣ ኢንተርኔቱን ሰጥቶ ቁጭ ማለት ብቻ ሳይሆን ምን እያየ/ች ነው የሚለውን መከታተል ይኖርባቸዋልም ባይ ናቸው።

« የሚገርምሽ ነገር ሰሞኑን ወደኛ ተቋም የ15 ዓመት ልጅ መጥቶ ነበር፤ ይህ ልጅ ደግሞ ትምህርት ቤት ሲሄድ አረቄ፣ ጅን ምናምን በትንንሽ ብልቃጦች እያደረገ በቦርሳው ይዞ ነው። ይህንን እናቱ አታውቅም። ግን ደግሞ ከፍ ያለ የባህርይ ለውጥ ያመጣ ጀመር። ነገሩ ሲጣራ ችግሩ ሌላ ሆኖ ተገኘ። እናት ይህንን ስትሰማ ራሷን ልትስት ነበር። በመሆኑም ልጆቻችንን ልንፈትሻቸው፣ ልናዋራቸው ፣ ልንቀርባቸው ይገባል። ስለ ሕይወትም ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ የእኛ ኃላፊነት ነው።» ሲሉም ከሥራቸው አኳያ ያለውን ሁኔታ በማንሳት ይመክራሉ።

እኛ ሁሉንም ነገር አትንኩ ብቻ ነው የምንላቸው ነገር ግን ሁሉንም በግልጽ መንገር ያስፈልጋል፤ እንዲፈሩን ሳይሆን እንዲያከብሩን ማድረግ ግድ ነው። ሌላው ደግሞ ልጄን ከሁሉም ነገር አርቄ ይዤ ማንንም ሳላገናኝ አሳድጋለሁ ማለቱም ጥሩ አይደለም። አንድ ቀን ሲወጡ የሚያርፉት ያ የተከለከሉት ነገር ላይ ነው። ስለሆነም ልጆቻችንን ጠዋትና ማታ ነው ማግኘትና ነባራዊ ሁኔታዎችን ማስረዳት ያለብን። እኛ ልጆቻችን የምናገኛቸው ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር ነው። ቤታቸው ውስጥ ያለ ችግርን እንኳን ቢኖር ለጓደኞቻቸው ነው የሚነግሩት ፤ በዚህ ጊዜ ጓደኞቻቸው የሚሏቸው ከጭንቀትሽ ለመውጣት ይህንን ኪኒን ዋጪ፤ ይህንን ጠጪ፤ እዚህ ቦታ ሂጂ ነው። ይህ ደግሞ ለልጆች ችግር ውስጥ መግባት ግንባር ቀደም ምክንያት ይሆናል። ስለዚህም ለልጆቻችን ጊዜና ፍቅርን መስጠት ከእኛ የሚጠበቅ ትንሹ ሀላፊነት ነውና ተጠያቂ እንዳንሆን በተቻለ መጠን ቤታችንን ሰላማዊ ማድረግ ይኖርብናል መልእክታቸው ነው።

### መልዕክት

አሁን ላይ በሱስ ዙሪያ ተረዳድተን ሰርተን ለውጥ ካላመጣን በየቤቱ ለቅሶ ይሆናል። ሁሉም ያለቅሳል፤ በመሆኑም በተለይ ቤተሰብ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ በእድሮች፣ በመስሪያ ቤቶች ላይ ሰፋ ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ያስፈልጋል። በእኛው ስህተት የተበላሹ ልጆቻችንን ከቤት አስወጥተን የጎዳና ተዳዳሪ የምናደርግ ብዙ ነን።

ሱስ ዛሬ ላይ ከቤተሰብ አልፎ እንደ ሀገር እየፈተነን ነው። ነገር ግን እኔ አንዳንድ መስሪያ ቤቶች እየሄድኩ እስቲ በዚህ ላይ እንስራ ይህንን አግዙን ብዬ በምጠይቅበት ጊዜ ‹‹ሀገራዊ ችግር ላይ ነን›› የሚል መልስ የሚሰጡ አሉ ፤ አዎ ሀገር ችግር ላይ ናት። ነገር ግን ትልቅ የሀገር ችግር የትውልዱ መጥፋት ነው። ይህ ትውልድ በዚህ ሁኔታ እያጣነው ከመጣን ማነው የሚተካው? የሚለውን ማሰብ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም እኔ በ60 ዓመቴ ይህችን ጠብታ እሰራለሁ። ሌላውም እንደዚሁ ቢተባበር ብንሰራ በጅምሩ ላይ ደግሞ መንግስት አይዟችሁ በርቱ ብሎ ደጀን ቢሆንልን ዘላቂ መፍትሔ እናመጣ ነበር።

እኛ የፈጀውን ጊዜ ፈጅተን ልጆቹን ከሱስ ካላቀቅን በኋላ የሚቀበላቸው፣ ስራ እንዲሰሩ የሚያግዛቸው ቢኖር ዳግም ወደሱስ ውስጥ እንዳይመለሱ እንደውም እነሱ ራሳቸው ሌሎችን እንዲያስተምሩ ይሆኑ ነበር። በመሆኑም ይህችን ጅማሮ ያየ መንግስት ማዕከሉ ተጠናክሮ የራሱን ስራ ፈጥሮ በራሱ ገቢ ተዳድሮ ለብዙዎች ለውጥ ምክንያት ይሆን ዘንድ ባለድርሻ አካላት ማየት ቢችሉ ሲሉ ሲስተር ጥሪያቸውን ያቀርባሉ።

**የሀገር ችግር የትውልዱ መጥፋት ነው። ይህ ትውልድ በዚህ ሁኔታ እያጣነው ከመጣን ማነው የሚተካው? የሚለውን ማሰብ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም እኔ በ60 ዓመቴ ይህችን ጠብታ እሰራለሁ። ሌላውም እንደዚሁ ቢተባበር ብንሰራ በጅምሩ ላይ ደግሞ መንግስት አይዟችሁ በርቱ ብሎ ደጀን ቢሆንልን ዘላቂ መፍትሔ እናመጣ ነበር።**

# እውነትና ፍትህ የሚተሳሰሩበት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት



**ዳግም ከበደ**

የኢትዮጵያ የእርቅና የሽምግልና ስርዓት ሰዎች በእርስ በርስ ግንኙነት የሚከሰቱ አለመግባባቶችን የሚፈቱበት ነው። ይሁን እንጂ ከመደበኛው የፍርድና የፍትህ ስርዓት ጎን ለጎን የብሔር ብሔረሰቦች ሀብትና እሴት በሆነው በዚህ ስርዓት የመዳኘትና አለመግባባቶችንና ግጭቶችን የመፍታቱ ልምድ የደበዘዘ እንደሆነ የብዙዎች እምነት ነው።

የእርቅ ስርዓቱ ግለሰቦች፣ ድንበር የሚጋሩ ህዝቦች፣ የፖለቲካ ልዩነት ያላቸው ቡድኖችና መሰል አካላት በመካከላቸው አለመግባባቶች ሲፈጠሩ፣ ግጭቶቹ ተባብሰው የከፋ ጥፋት እንዳያደርሱ በሰከነ መንፈስ ተወያይቶ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከመደበኛ የፍርድ ስርዓት ጎን ለጎን ድርሻው ከፍተኛ እንደሆነም ይነገራል። ኢትዮጵያም ይህን መሰል ስርዓትን የያዙና በአገር ሽማግሌዎች፣ በባህላዊ መሪዎችና ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች የሚመሩ ሽንጎዎችና የእርቅ ስርዓቶች ያላት አገር ነች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በዜጎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች በዚሁ ስርዓት መፈታት ሲገባቸው በተቃራኒው ጥቃቅን ግጭቶች ተባብሰው በመቀጠል ለሰው ሕይወት መጥፋት፣ ለንብረት መውደምና ለዝርፊያ ምክንያት እንደሆኑ ተገልጿል። መንግስትን ጨምሮ የተለያዩ አካላት በግልም ሆነ በጋራ ይህንን እሴት ለማጎልበት እንዲሁም የመፍትሄ አካል ለማድረግ በተለያየ ጊዜ ጥረት ያደርጋሉ።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የባህልና ቱሪዝም አምድ ላይ "ባህላዊ የሽምግልና ስርአቶቻችንን በየጊዜው ለሚከሰቱ አለመግባባቶች መፍትሄ እንዲሆኑ ምን መስራት ይኖርብናል?" በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ አተኩሯል። ከሰሞኑም በአፍሪካ የአህጉር በቀል አመራር ምክር ቤት ብሔራዊ የባህል መሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ የአገር ሽማግሌዎች በተገኙበት በአዲስ አበባ፣ ስለተደረገ ምክክር ጥቂት ሃሳቦችን እናነሳለን።

አፍሪካ የአህጉር በቀል አመራር ምክር ቤት ማኔጂንግ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ቡሩክ ተመስገን ብሔራዊ የባህል መሪዎች ፎረም የማቋቋም አላማውን በተመለከተ ሲናገሩ፤ ‹‹በአገራችን በልዩ ልዩ አካባቢዎች በርካታ ግጭቶች ይከሰታሉ። ምክር ቤታችን በሰራው ጥናት መሰረትም ‹ግጭቶቹ እየተስፋፉና ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ የመጡት የባህላዊ ስርዓቶቻችንን ወደጎን በመተዋችን ነው› የሚል ሳይንሳዊ ግኝት አለን። ከምንም በላይ ሰዎችን ሊይዛቸውና ሊገዛቸው የሚችለው ባህላቸው ነው። የባህላዊ መሪዎችና ሽማግሌዎች ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ እድሉ ባለመመቻቸቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ግጭቶች ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ መምጣታቸውን ጥናታችን ያመለክታል›› ይላሉ።

"ባህላዊ መሪዎችን እንዲሁም ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን ወደ ቦታቸው ብንመልስ አብዛኛዎቹ አለመግባባቶችና ጥፋት የሚያደርሱ ክስተቶች በቶሎ ጥፋት ሳያደርሱ መፍትሄ ያገኛሉ ብለን እናምናለን" የሚሉት ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ፤ በዚህ ወቅት ይህንን እሴት ጉልህ ሚና እንዲጫወት ማድረግ ተገቢ መሆኑንም ይጠቁማሉ። ምክር ቤታቸውም ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን የሚመሩ የባህል መሪዎች ይህንን ሚና መጫወት እንዲችሉና በአገሪቱ የተከሰቱት ልዩ ልዩ አለመግባባቶች መፍትሄ እንዲያገኙ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ እንደሆነ ይናገራሉ።

አቶ ቡሩክ ‹‹በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በሰራነው ጥናት በአንዳንድ ቦታዎች እስከ 62 በመቶ፣ በአንዳንዶቹ አካባቢዎች ደግሞ እስከ 96 በመቶ ድረስ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት እና ባህላዊ መሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አላቸው›› ይላሉ፡፡ ህብረተሰቡ ለዚህ መሰል አገር በቀል እሴት ልቡ ክፍት እንደሆነና ተግባራዊ ቢሆን ደስተኛ እንደሆነ ይናገራሉ።

እርሳቸው እንደሚገልጹት፣ ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በመተባበር በክልሎች (ደቡብ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሱማሌ፣ አማራ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና አሮሚያ) ክልሎች ዋና ከተሞች ላይ በመገኘት ከየክልሉ ለ15፣ በአጠቃላይ ለ150 ባህላዊ መሪዎች የአምስት ቀናት ስልጠና ከግንቦት 2014 እስከ ኅዳር 2015 ድረስ ለ6 ወራት ሰጥተው አጠናቅቀዋል፡፡ ከባህል መሪዎቹ በተነሳ ጥያቄ መሰረት የባህል መሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ህጋዊ ሂደቶችን ለመጨረስ ከስምምነት ላይ ተደርሷል። በየክልሉ የሚገኙ የአገር ሽማግሌዎችም እርስ በእርስ እንዲገናኙና በተደራጀ መንገድ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ማህበራት እንዲመሰርቱ የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል። ከክልል አልፎ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመንቀሳቀስም "ብሔራዊ የባህል መሪዎች ምክር ቤት" ለማቋቋም እየተሰራ ነው።

ዶክተር መልሰው ደጀኔ በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት እንዲሁም የልማት ጥናት ረዳት ፕሮፌሰርና ተመራማሪ ናቸው። አፍሪካ የአህጉር በቀል አመራር ምክር ቤት፣በቱሪዝምና ባህል ሚኒስቴር እንዲሁም በዩኤስ ኤይ ዲ (USAID) ድጋፍ የኢትዮጵያ የባህል መሪዎች ለአገር ግንባታ (ሰላምን ለማስፈን) ያላቸውን ሚና ለማጎልበት ስልጠናዎችን በመስጠትና በማስተባበር ይሰራሉ። እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ ለባህል መሪዎች ስልጠናዎችን ለመስጠት እንዲሁም የጋራ ምክር ቤት ለመመስረት በተለያዩ ክልሎች በሚዘዋወሩበት ጊዜ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግጭቶች እንዳሉ ተረድተዋል። ይህም እንደ አገር "አዎንታዊ ሰላም" አለመስፈኑን እንዳስገነዘባቸው ይገልፃሉ።

‹‹የእነዚህን ግጭቶች ስረ መሰረታቸውን ስንመረምራቸው ‹አገር በቀል እውቀቶች ምን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ› የሚለው ዋናው ትኩረት መሆን ይገባዋል፡፡ በኢትዮጵያ የትኛውም አካባቢ ከምስራቅ ጫፍ እስከ ምእራብ መሄድ ቢቻል አገር በቀል እውቀትና የግጭት አፈታት ስርዓት እውነትና ፍትህ የሚተቃቀፉበት ስርዓት ሆኖ መመልከት እንችላለን›› በማለት ትዝብታቸውን ይናገራሉ።

‹‹አለመግባባትን ወደ ፍርድ ቤት ይዞ መሄድ ቢቻል ፍትህ አገኘን ማለት እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ ፍትህ ሁልጊዜ እውነትን ላይዝ ይችላል፡፡ አንድ አካል ባመረተው መረጃና ባቀረበው ሰነድ ልክ በዚያ ተመስርቶ ነው ዳኝነት የሚያገኘው። በአብዛኛው ከደሃ ይልቅ ሃብታም፤ ከተራ ሰው ይልቅ ባለስልጣን አልያም ሰፊ እድል ያለው ሰው መረጃን የማምረት አቅሙ አለው። ወደ ባህላዊው የግጭት አፈታት ስርዓት በምንሄድበት ጊዜ ግን ፍትህ እውነት ማለት ነው፤ ማንኛውም ሰው በየትኛውም የስልጣን፣ የሀብት፣ የዝናና የተፅእኖ ፈጣሪነት ደረጃ ላይ ቢሆንም በባህላዊው ስርዓት ከተራው ሰው እኩል ዳኝነትን ያገኛል፡፡ ባህላዊ መሪዎች እና ሽንጎ ፊት ተይዞ የሚቀርበው እውነትን ያዘለ መረጃ ካልሆነ መርገምን፣ ከማህበረሰብ መገለልንና የመሳሰሉት ቅጣቶችን ይዞ ይመጣል›› ይላሉ።

"በኢትዮጵያ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ቢኖርም የጎለበተ አይደለም" የሚሉት ዶክተር መልሰው፤ ብዙ ውጥንቅጦቻችንን የምንፈታው በዚሁ ባህላዊ በሆነው የግጭት አፈታት ስርዓት ቢሆንም በትኩረት አልሰራንበትም ይላሉ። ይሁን እንጂ ለመንግስት፣ ለፍትህ ስርዓቱና በጥቅሉ ለህግ ያስቸገሩ ጉዳዮች በባህል መሪዎችና ሽማግሌዎች በጥቂት ጊዜ መፍትሄ ሲያገኙ መመልከት ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ አለመሆኑንም ያነሳሉ።

"የባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት፣ የጋራ አሸናፊዎች መስተጋብር ነው" የሚሉት ዶክተር መልሰው፤ አጥፊም ሆነ ተጠቂ አሸንፈው የሚወጡበት ስርዓት እንደሆነ ይናገራሉ። ፍርድ ቤት በመሄድ ፍትህ ማግኘት ቢቻልም "የቂም በቀለኝነቱን ሽክርክሪት" የሚሰብር አለመሆኑን በመግለፅም ሙሉ እርቅና ግጭትን ማስወገድ የሚያስችለው በባህል መሪዎች አማካኝነት በሚተገበረው የግጭት አፈታት ስርዓት መሆኑንም ይገለፃሉ።

የአፍሪካ የአህጉር በቀል አመራር ምክር ቤት ባመቻቸው እድል የክልሉን ሽማግሌዎች በመወከል የባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓትን በተመለከተ ምክክር ለማድረግና በሀገር አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ የጋራ የባህል መሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ከአማራ ክልል፣ ጎንደር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ለአምስት ተከታታይ ቀናት ግጭቶችን በሽምግልና መፍታትን በሚመለከት ስልጠና የወሰዱት አቶ አዳነ አዳምሰገድ የመጡበት ክልልም ግጭትና አለመግባባት ሲከሰት ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የተለያየ የሽምግልና ስርዓት እንዳለ ይናገራሉ። በዚህ መሰረት ችግሮች ሲቃለሉ መቆየታቸውንም ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ ምክር ቤቱ ባመቻቸላቸው እድል መሰረት አንድና ወጥነት ያለው፣ ተፅእኖ መፍጠር የሚችል፣ መምከር፣ ማስተማር እንዲሁም ተቆጥቶ ሊያርም የሚችል የሽምግልና ማህበር እንዳቋቋሙ ይናገራሉ።

"በቅማንትና በአማራ አካባቢ የነበሩ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን ለመፍታት ሽምግልና ትልቅ ሚና ነበረው። አሁንም ድረስ በጎ ተፅእኖ እየፈጠርን እንገኛለን" የሚሉት አቶ አዳነ አዳም ሰገድ፤ ‹‹ወደ አንድነት እንድንመጣ የተሰደዱና ወደ በረሃ የገቡ ወደ ቀያቸው ገብተው ሰላም እንዲፈጥሩ በዚህ በባህላዊ ግጭት አፈታት ስርዓት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው›› ይላሉ።

አቶ ተስፋዬ ደነቀ የአፍሪካ የአህጉር በቀል አመራር ምክር ቤት ያመቻቸውን የምክክር መድረክ ለመካፈል ከሲዳማ ክልል ተወክለው የመጡ የአገር ሽማግሌ ባህላዊ መሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ግጭቶች ሲከሰቱ በባህላዊ መሪዎች ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣትና ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት እንዲኖር የሚደረገው ጥረት ተገቢ ነው። በዚህ እረገድ አህጉር በቀል አመራር ምክር ቤቱ እየሰራ ያለውን ተግባር አድንቀዋል።

"በሲዳማ ክልል ባህላዊ የግጭት አፈታት የተመረጠ ሲሆን በግለሰብም ሆነ በቡድን ለሚነሱ አለመግባባቶች በሽምግልናና በልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች መፍትሄ ይሰጣል" የሚሉት የአገር ሽማግሌው አቶ ተስፋዬ ደነቀ፤ ይህንን ማድረግ የሚችል ባህላዊ አቅምና ስርዓት ማጎልበት እና ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ይላሉ። እርሳቸውን ጨምሮ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የመጡ የአገር ሽማግሌዎችም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በባህላዊ እሴቶች፣ እውቀቶች እና ሀብቶች ለመፍታት እንዲያስችላቸው የጋራ የባህል መሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ይናገራሉ። መንግስትም ይህን መሰል በጎ ሃሳብ እና ምግባር መደገፍ እና ተቋማዊ ሆኖ እንዲቀጥል እውቅና መስጠት እንደሚገባውም ይገልፃሉ።

## እንደ መውጫ

ኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ከራሷ አልፎ ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች ሰላምን ለማውረድ የሚጠቅሙ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች እንዳሏት ይነገራል። እነዚህን ባህላዊ እሴቶች ከዘመናዊ የህግ ስርአት ጋር በማቀናጀት መስራት እንደሚገባ የተለያዩ ምሁራን እና ተቋማት ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ። ከእነዚህ መካከል ብሔራዊ የባህል መሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ላለፉት አንድ ዓመታት እንቅስቃሴ እያደረገ የሚገኘውና በእሴቶቹ ዙሪያ ስልጠና እየሰጠ ያለው የአፍሪካ የአህጉር በቀል አመራር ምክር ቤት አንዱ ነው፡፡

አገር በቀል የሽምግልና ባህልን ተጠቅሞ ግጭቶችን ለመፍታት የሚደረግ ጥረት በመንግስት በኩል ቢኖርም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አካቶ ተቋማዊ በሆነ መልኩ ማስኬድ አሁንም ድረስ በበቂ ሁኔታ ተሰርቶበታል ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም የእሴቱ ባለቤት የሆኑ እናቶች እና አባቶች፣ ምሁራን፣ የባህልና ቱሪዝም ተቋማት፣ ህግ አውጪዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት እንዲዳብር መስራት ይኖርባቸዋል የዛሬው መልእክታችን ነው። ይህን ማድረግ ሲቻል እውነትና ፍትህ የሚተሳሰሩበት ጠንካራ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን መዘርጋት እንደሚቻል እናምናለን።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ኢትዮጵያን የወደደችውና ኢትዮጵያውያን የወደዷት ዓለም አቀፍ እንስት

**ዋለልኝ አየለ**

«ስም ከመቃብር በላይ ይውላል» ይባላል። ታዲያ ስም ከመቃብር በላይ የሚውለው ሰውየው/ሴትዮዋ በሰሩት ሥራ ነው እንጂ የማንኛውም ሰው ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ማለት አይደለም። ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ሲባል፣ ሰውየው/ሴትዮዋ በሰሩት ሥራ ስማቸው ሲዘከር ይኖራል ማለት ነው።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 99 ዓመታት ወደኋላ እንመለሳለን። ተመልሰንም አንዲትን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ባለውለታ እናስታውሳለን። የአንዳንድ ሰዎች መወለድ እንዲህ ነው። ከራስ አልፎ ለቤተሰብ፣ ከቤተሰብ አልፎ ለማህበረሰብ፣ ከማህበረሰብ አልፎ ለአገር፣ ከአገር ሁሉ አልፈው ዓለም አቀፍ ዜጋ የሚሆኑ አሉ።

ከ99 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 16 ቀን 1916 ዓ.ም(በፈረንጆቹ ጃንዋሬ 24, 1924) ካትሪን ሐምሊን የተባለች እንስት በአውስትራሊያ ሲድኒ ተወለደች። ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ዕድሜዋን ያሳለፈችው ለኢትዮጵያ በመሥራት እና ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ነው። እነሆ ዛሬ ይቺን ጀግና ነው የምናስታውስ።

ሐምሊን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በኒው ሳውዝ ዌልስ ግዛት ውስጥ በሚገኝ ትምህርት ቤት ካጠናቀቀች በኋላ ሲድኒ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ቤት ገብታ የሕክምና ትምህርት አጠናች። የልምምድ ቆይታዋን ቅዱስ ዮሴፍ እና ቅዱስ ጊዮርጊስ በተባሉ ሆስፒታሎች አጠናቀቀች። ከዚያም «ክራውን ስትሪት» ወደተባለው የሴቶች ሆስፒታል ገብታ የሁልጊዜም ምኞቷ የነበረውን ሴቶችን የመርዳት ተግባሯን ጀመረች። በዚህ ወቅት ነበር ከዶክተር ሬጂናልድ ሐምሊን ጋር የተዋወቁትና ትዳር የመሰረቱት።

በ1951 ዓ.ም ጥንዶቹ ዶክተሮች የኢትዮጵያ መንግሥት የአዋላጅነት ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ለመክፈት ያለውን ፍላጎት የሚገልፅ ማስታወቂያ ተመለከቱ። ሪቻርድ ከተባለው የስድስት ዓመት ልጃቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ተቋሙን የማቋቋም ኃላፊነትን ተረከቡ። ለሦስት ዓመታት ቆይታ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት እነዚህ ጥንዶች እስከዕለተ ሞታቸው ድረስ በኢትዮጵያ ይቆያሉ ብሎ የገመተ አልነበረም።

ጥንዶቹ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ስራቸውን የጀመሩት በልዕልት ጸሐይ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ ነበር። በወቅቱ እነካትሪን የተመለከቱት በወሊድ ወቅት በሚከሰት ችግር (ፌስቱላ) ምክንያት የሚሰቃዩ ሴቶች መከራ ፈፅሞ ያልጠበቁት ሆኖባቸው ነበር። እነርሱ ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት የፌስቱላ ችግር ያለባቸው ሴቶች፣ እንኳን ተገቢውን ሕክምና ማግኘት ይቅርና እንደሰው የሚቆጥራቸው አጥተው የሚደርስባቸው መገለል እጅግ በጣም አስከፊ ነበር።

እንዲህ ዓይነት ስቃይ ከዚህ ቀደም አጋጥሟቸው የማያውቁት ጥንዶቹ ዶክተሮች የራሳቸውን የሕክምና መመሪያ በማዘጋጀት የኢትዮጵያውያኑን ሴቶች ሕይወት የመታደግ ተግባራቸውን ጀመሩ። ተግባራቸው በሰዎች ዘንድ ሲሰማ በርካታ ሴቶች ለሕክምና መጉረፍ ጀመሩ። በመጀመሪያ ልዕልት ጸሐይ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ 10 አልጋዎች ያሉት ክሊኒክ አቋቋሙ። በግንቦት 1968 ዓ.ም ደግሞ የአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታልን ከፈቱ።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1993 የዶክተር ሬጂናልድ ሐምሊን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ለባለቤታቸው ዶክተር ካትሪን ሐምሊን ከባድ ፈተና ሆነባቸው። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያውያን ሴቶች ስቃይ ከሁሉም ነገር በላይ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን የተረዱት ዶክተር ካትሪን ሐምሊን ሐዘኑን ተቋቁመው ሴቶችን የመርዳት ተግባራቸውን ቀጠሉ።

የዶክተር ካትሪን ሴቶችን የመርዳት ተግባራቸው ሴቶቹን በማከም ላይ ብቻ የተገደበ አልነበረም። አዋላጅ ነርሶችን የማሰልጠን ሕልማቸውን ለማሳካት በ2000 ዓ.ም የሐምሊን አዋላጅ ነርሶች ማሰልጠኛ ኮሌጅ እንዲቋቋም አድርገዋል። አዋላጅ ነርሶቹ ስልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በገጠራማ የኢትዮጵያ ክፍሎች በሚገኙ ክሊኒኮች ተመድበው ያገለግላሉ። የአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የፊስቱላ ችግር ተጠቂዎች ካሉባቸው አገራት የሚመጡ ሰልጣኞችንም ያስተምራል። ከነዚህም መካከል የኬንያ፣ የኮንጎና የባንግላዴሽ ባለሙያዎች ይጠቀሳሉ።

ዶክተር ካትሪን ለታማሚዎቻቸው በሚሰጡት የህክምና ዓይነት በእጅጉ እንደሚኮሩና እንደሚደሰቱ ይናገሩ ነበር። « ... ችግሩ የተከሰተበትን(ሕመም የሚሰማበትን) ቦታ ብቻ አናክምም፤ ሕክምናችን ለታማሚው ሙሉ ፈውስ የሚሰጥ የፍቅር፣ የእንክብካቤና የግንዛቤ ሕክምና ነው ...» ብለዋል። በዚህ ሕክምናቸውና በአጠቃላይ የበጎ አድራጎት ስራዎቻቸው ምክንያት ከፊስቱላ ችግር ተላቀው መደበኛ ሕይወታቸውን የሚኖሩት ብቻም ሳይሆኑ ዶክተር ካትሪንን የሚያውቋቸው ሁሉ «እማዬ» እያሉ ይጠሯቸው ነበር።



ዶክተር ካትሪን ሐምሊን

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በመባል የሚታወቀው ማዕከል ከ550 በላይ ሰራተኞችን (አብዛኞቹ በዶክተር ካትሪን ሐምሊን የሰለጠኑ)፣ ስድስት ሆስፒታሎችን፣ «ደስታ መንደር» የተባለ የማገገሚያ ማዕከልን፣ የሐምሊን አዋላጅ ነርሶች ማሰልጠኛ ኮሌጅን እንዲሁም በሐምሊን የሚታገዙ 80 የማዋለጃ ክሊኒኮችን አስተሳስሮ የያዘ ተቋም ሆኗል። ማዕከሉ ፊስቱላን ከማከም በተጨማሪ ችግሩ እንዳይከሰት አስቀድሞ የመከላከልና ከችግሩ የተላቀቁ ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና የበቁ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል።

በኢትዮጵያ ስድስት የሐምሊን ፊስቱላ ሆስፒታሎች ይገኛሉ። ይህም ብዙዎቹ የፊስቱላ ታማሚዎች በገጠራማ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን የችግሩ ተጠቂዎች በተነፃፃሪነት በአቅራቢያቸው አገልግሎት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። በእነዶክተር ካትሪን ሐምሊን ጥረት ባለፉት ከ60 በላይ ዓመታት በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች በወሊድ ወቅት በሚከሰት ችግር (ፊስቱላ) ምክንያት ከገቡበት መከራ እንዲወጡ አድርገዋል።

ዶክተር ካትሪን ሐምሊን በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2001 ጆን ሊትል ከተባለ አውስትራሊያዊ ጋዜጠኛ ጋር በመተባበር «The Hospital By the River: A Story of Hope» በሚል ርዕስ የሕይወት ታሪካቸውን ጽፈው አሳትመዋል። በዚህ መጽሐፋቸው ላይም የእርሳቸውና የባለቤታቸው ተግባር «በስቃይ ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች ከሚደረጉ እርዳታዎች መካከል አንዱ ነው» በማለት ገልጸውታል። በአውሮፓውያኑ 2016 የታተመው የመጽሐፉ ሁለተኛ እትም ቀዳሚ ቃል የተፃፈው በወቅቱ በአውስትራሊያ የንግሥት ዳግማዊት ኤልሳቤጥ ወኪል በሆኑት ኩዊንቲን ብራይስ ነው።

ሕይወታቸውን ሁሉ ሰዎችን ማዳን የሆኑት እኚህ ሰው ለመሆኑ ምን እውቅና ተሰጣቸው? ከተባለ፤ ምንም እንኳን ሥራቸውን ይመጥናል ባይባልም የሚከተሉትን በርካታ እውቅና እና ሽልማቶች አግኝተዋል።

ዶክተር ካትሪን ሐምሊን በዋጋ ለማይተመነው አበርክቷቸው በርካታ ሽልማቶችንና ክብሮችን ተቀዳጅተዋል። ከእነዚህም መካከል፡-

- **የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሰብዓዊነት ሽልማት**
- **የኦርደር ኦፍ አውስትራሊያ ሽልማት**
- **የአውስትራሊያና ኒውዚላንድ ጦር ዘማቾች የሰላም ሽልማት**
- **የታላቁ የቅዱስ ጊዮርጊስ የላቀ የወርቅ ሜዳልያ ሽልማት**
- **የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ኮሌጅ የክብር የወርቅ ሜዳልያ ሽልማት**
- **የዞንታ ዓለም አቀፍ ሽልማት**
- **የሮተሪ ኢንተርናሽናል የሰላም ሽልማት**
- **የአሜሪካ የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ኮሌጅ የክብር ሽልማት**
- **የአውስትራሊያ ከፍተኛ ብሔራዊ ሽልማት**
- **የዓለም አቀፍ የጤና ምክር ቤት የላቀ አፈፃፀም ሽልማት**
- **የኤደንብራ የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ኮሌጅ የክብር ሽልማት**
- **የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስነ ሕዝብ ሽልማት**
- **የአሜሪካ ሕክምና ማኅበር/የዶክተር ናታን ደቪስ ዓለም አቀፍ የጤና አጠባበቅ ሽልማት**
- **የሲዲኒ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ሽልማት**
- **የአውስትራሊያ አስተማሪዎች ኮሌጅ የክብር ሽልማት**
- **የእንግሊዝ ሕክምና ማኅበር ሽልማት**
- **የምርጥ የሰብዓዊና የማኅበራዊ አገልግሎት ሽልማት (ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝደንት)**
- **የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ሽልማት**
- **የሰዎች ለሰዎች ድርጅት የሕይወት ዘመን ሽልማት**
- **የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የላቀ አፈፃፀም ሽልማት (ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝደንት)**
- **የዓለም የስርዓተ ፆታ ማኅበር የወርቅ ሜዳልያ ሽልማት**
- **የአውስትራሊያ ሕክምና ማኅበር ሽልማት**
- **የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአውስትራሊያ ማኅበር ሽልማት**
- **የ2009 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት**

ተጠቃሾች ናቸው። ከእነዚህ ሽልማቶች በተጨማሪም ዶክተር ካትሪን ሐምሊን በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር የ1999 እና የ2014 የኖቤል የሰላም ሽልማት እጩ ሆነው ቀርበው ነበር። በ2009 ዓ.ም ተለዋጭ ኖቤል በመባል የሚታወቀውና አስቸኳይ ምላሽ ለሚሹ ዓለም አቀፍ ችግሮች ተግባራዊና ተምሳሌታዊ የሆኑ መፍትሄዎችን ላፈለቁ አካላት የሚሰጠው የ«ራይት ላይቭሊሁድ» ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በ2004 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ የክብር ዜግነት ተሰጥቷቸዋል። በወቅቱ የኢትዮጵያ ፓስፖርትና የክብር ዜግነት የምስክር ወረቀት ለዶክተር ካትሪን የሰጡት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ «በኢትዮጵያ የፊስቱላ ሕመም ሰለባ ለሆኑ ሴቶችና እናቶች የተለየ ፍቅርና ሕክምና በመስጠት ለረጅም ዓመታት የሚደነቁ ተግባራትን ያከናወኑት ዶክተር ካትሪን ሐምሊን ከኢትዮጵያውያን አንዷ መሆን መቻላቸው የሚያኮራ ነው» ብለው ነበር።

ዶክተር ካትሪን ሐምሊን በበኩላቸው፤ «ኢትዮጵያ ባልወለድባትም ከትውልድ አገሬ የበለጠ እወዳታለሁ ... አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለአገሪቱና ለሕዝቧ ያለኝን ፍቅርና አክብሮት ተገንዝቦ የክብር ዜጋ እንዲሆን ስለፈቀደልኝ ከምንም ነገር በላይ ደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል። ... የተሰጠኝ የክብር ዜግነት የጀመርኩትን የሰብዓዊና የሕክምና አገልግሎት ዘላቂነት እንዲኖረው የሚያደርግ ኃላፊነት ጥሎብኛል ...» ሲሉ ተናግረው ነበር።

በአውሮፓውያኑ 2011 በእንግሊዝ ንግሥት ዳግማዊት ኤልሳቤጥ የክብር የምሳ መርሃ ግብር ላይ እንዲታደሙ ከተደረጉ 50 ታላላቅና ተፅዕኖ ፈጣሪ አውስትራሊያውያን መካከል አንዷ ዶክተር ካትሪን ሐምሊን ነበሩ። በ1996 ዓ.ም በኦፕራ ዊንፍሬይ የቴሌቪዥን ዝግጅት ላይ ቀርበው ተሞክሯቸውን አስረድተዋል። ይህም ዝነኛዋ አሜሪካዊት ኦፕራ ዊንፍሬይ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታልን እንድትጎበኝና «A Walk to Beautiful» የተሰኘ ዘጋቢ ፊልም እንድትሰራ አስችሏታል።

በጋዜጠኝነት ሙያ ከፍተኛ ቦታ ካላቸው ሽልማቶች መካከል አንዱ የሆነው የፑሊትዘር ሽልማት አሸናፊው አሜሪካዊው ጋዜጠኛ ኒኮላስ ክሪስቶፍ ዶክተር ካትሪን ሐምሊንን «የወቅቱ እናት ቴሬዛ» በማለት ገልጿቸዋል።

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በግንቦት 2011 ዓ.ም የዶክተር ካትሪን ሐምሊንና የባለቤታቸውን የዶክተር ሬጂናልድ ሐምሊን የመታሰቢያ ሐውልትን በመረቁበትና ለዶክተር ካትሪን ሐምሊን የወርቅ ሽልማት ባበረከቱበት ወቅት ባደረጉት ንግግር « ... ዶክተር ካትሪን ከእኔ ዘር ውጭ አላይም የሚል አመለካከት በበዛበት በአሁኑ ወቅት ከዘር፣ ከቀለም፣ ከጾታ በላይ ሰውነትንና ሰውን ማዳን ያሳዩ እናት ናቸው። ህዝቡ ከእርሳቸው ተግባር መማር ይገባዋል፤ እኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትም እንደዚህ ዘመን የማይሽረው ለትውልድ የሚጠቅም አሻራ ለማስቀመጥ መስራት ይጠበቅብናል ... ዶክተር ካትሪን እ.አ.አ ከ1959 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት ስልሳ ዓመታት ከስልሳ ሺህ በላይ እናቶችንና ሴቶችን መታደግ ችለዋል። ይህ ደግሞ 60 ሺህ ተገድሎ በሚጨፈርበት ሀገር 60 ሺህ ያዳኑ የድሀ እናት የሚያስብላቸው መልካም ስራቸው ነው ... » ብለው ነበር።

የካትሪን ሐምሊን ፊስቱላ ፋውንዴሽን ሊቀ መንበር ጁሊ ዋይት « ... ካትሪን በበርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ሕይወት ላይ ትልቅ ለውጥ የፈጠሩና አስደናቂና ሰብዓዊ የሆነ ሕይወት የኖሩ ሰው ናቸው። ሴቶችንና እናቶችን ለማገልገል ያላቸው በፍቅር የተሞላ የአገልግሎት ተነሳሽነትና ጠንካራ ጥረት ሁላችንንም የሚያኮራና ልንማርበት የሚገባ ታላቅ ገድል ነው ...» ብለዋል።


የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ማሞ ደግሞ « ... ዶክተር ካትሪን ላበረከቱት የሕይወት ዘመን አስተዋጽኦ ከልብ እናመሰግናለን። እርሳቸው የጀመሩትን ፊስቱላን ከኢትዮጵያ ምድር ጨርሶ የማጥፋት ርዕይ እውን ለማድረግ ተግተን እንደምንሰራ ቃል እንገባለን» በማለት ተናግረው ነበር። ሌሎችን ሰዎች ሁሉ ለእንዲህ አይነት በጎ ነገር አነሳስተዋል፤ ጀግና ፈጥረዋል ማለት ነው።

በ60 ዓመታት ወርቃማ የኢትዮጵያ ቆይታቸው ከ60 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሕይወት የሰጡት አንጋፋዋ የፅንስና የማህጸን ስፔሻሊስት ሐኪም ዶክተር ኤሊኖር ካትሪን ሐምሊን በ96 ዓመታቸው መጋቢት 9 ቀን 2012 ዓ.ም ከ60 ዓመታት በላይ በኖሩባትና ባገለገሏት ኢትዮጵያ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። እነሆ ስማቸውና ሥራቸው ግን ከመቃብር በላይ ነው።

# የዝነኞች ገጽ

# የጎጃሙ የባህል አምባሳደር

**በሙሉጌታ ብርሃኑ**




ሙዚቃ ትዝታና ትውስታ ቀስቃሽ ምናባዊ የሕይወት ስዕል ነው። በክስተቶችና በልዩ ልዩ በዓላት መካከል የሚፈጠሩ ሙዚቃዎች የምንወዳቸው አይነት ሆነው ሲገኙ ደግሞ ብዙውን ጊዜ አድምጠን የማንጨርሳቸው፣ የተዘፈኑበት በዓላት በመጡ ቁጥር ሁሉ አብረን የምናስታውሳቸው ይሆናሉ።

በዓላትና ሙዚቃ፣ ሙዚቃና በዓላት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ለማለት ያስደፍራል። በዓላት ያለ ሙዚቃ ፈጽሞ አይደምቁም፤ በተለይ የጥምቀት በዓል ደግሞ የማይታሰብ ነው። በዓልን ያለሙዚቃ ማክበር ጨው የሌለው ምግብ እንደመመገብ ነውና አይጣፍጥም። ታዲያ ባሳለፍነው የጥምቀት በዓል በእስክስታ ትከሻችንን እየወዘወዝን፣ አንገታችንን እየነቀነቅን ወገባችን እስኪንቀጠቀጥ በብዙ ሙዚቃዎች ተውረግርገናል፣ ጨፍረናል። ነገር ግን ከሙዚቃም ሙዚቃ መርጠን በልዩነት አንድ ሙዚቃ እናስታውሳለን፤ የጥምቀት በዓል አንድ አካል እስከሚመስል ድረስ በየአመቱ እንደ አዲስ እየሰማን እንደ አዲስ ዳንኪራ የምንመታበት፣ ገና ጥምቀት ሲመጣ ሙዚቃው ትዝታና ትውስታ እየሆነ በጆሯችን የሚንቆረቆር አንድ የጥበብ ሰው አለ። መቼም እኔ ገና ዳር ዳሩን ስሄድ ይህንን ሙዚቃና የጥበብ ሰው ማንም ቀድሞ እንደሚገምተው አልጠራጠርም።

አዎ እሱ ነው፤ ‹‹ዘገሊላ›› ይህንን የማያስታውስ ማን ይኖራል? ባለቅኔው ዜመኛ ይሁኔ በላይ ተጨንቆና ተጠቦ ዘመን አይሽሬ የጥምቀት ስጦታ ከ18 አመታት በፊት 1997 ዓ.ም የጥምቀት ዋዜማ ላይ አበርክቷልና በየአመቱ አይሰለችም ሳይሆን ገና አይጠገብም።

'የዘገሊላ ዕለት፣ የዘገሊላ ዕለት
ነይልኝ በኔ ሞት
ለአስተሰርዮ ማርያም፣ ለአስተርዮ ማርያም
እመጣለሁ እኔም
በዓል ነው፣ በዓል ነው
አ በዓል ነው

በዓል ነው፣ ልንገናኝ ነው' እያለ ውብና ማራኪ በሆነ ድምጹ ይሁኔ ያዜማት ዜማ የጥምቀት በዓል ልዩ መታወቂያ እስከመሆን በቅታለች። እኛም በዛሬው የዝነኞች ገጽ አምዳችን ይህን በይሁኔ በላይ ሌሎች ስራዎችና የሕይወት ገጽታዎች ላይ ትኩረት እናደርጋለን።

የአባይ ወንዝ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሙዚቀኞች መፍለቂያ ከሆነችው ከጎጃሟ ፍኖተ ሰላም ፈልቆ የወጣው ይሁኔ በላይ ከልጅነቱ ጀምሮ በተለያዩ ክበባትና የሙዚቃ ባንዶች የሙዚቃ ክህሎቱን እያሳደገ በውጣውረዶች መሃል ትልቅ ስኬት ላይ መድረስ የቻለ ድምጻዊ ነው። የይሁኔ ሙዚቃዎች አብዛኞቹ ካያቸውና ከሰማቸው እንዲሁም ራሱ ከኖረው ሕይወት የመነጩ በመሆናቸው ቁልጭ ብለው የተቀመጡ የማህበረሰቡ የስሜት ነጸብራቅ ናቸው። ያደገበትን ባህል፣ ወግና ስርዓት በየሙዚቃዎቹ ውስጥ በማሳየትና በየትኛውም ቦታ የማህበረሰቡ የፊት ደጀን ሆኖ በቆራጥነት የሚቆም በመሆኑ ‹‹የጎጃም አምባሳደር›› የሚል ቅጽል ስም ለማግኘት በቅቷል።

እንዲህና እንዲያ እያለ የሰነበተው የጎጃሙ አምባሳደር የሙዚቃ ችሎታውን በማሳደግ የመጀመሪያ ስራው የነበረችውን ‹‹አንቱዬዋ›› የተሰኘውን ሙዚቃ ከሰማኸኝ በለው ጋር በጋራ በመሆን ለመስራት ቻለ። ሙዚቃው በድራማ የተሞላና በግሩም ዝግጅት የቀረበ ስለነበረ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትና ተደማጭነትን አጎናጸፈው። በዚህ ሙዚቃ ውስጥ ይሁኔ ያለውን አቅምና ልዩ ተሰጥኦ በሙሉ ለመጠቀም ሞክሯል። ማራኪ ከሆነው ድምጹ ፊት ለፊት ያለው ሙዚቃዊ እንቅስቃሴው ሙሉ ለሙሉ ባህልን የተላበሰ፣ ከዜማና ግጥሙ ጋር የተናበበ ስለነበረ ከማህበረሰቡ አልፎ በመላው ኢትዮጵያ ተቀባይነትን አገኘ።

ሙዚቃን በግሉ መስራት ከመጀመሩ በፊት ይሰራበት የነበረበት ግሽ አባይ ባንድ የሙዚቃን ምንነት የተረዳበትና የሙዚቃን ምሉእነት ተገንዝቦ የሕይወቱን የወደፊት የጉዞ ስንቅ የሸከፈበት እንደሆነ ይሁኔ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተናግሯል። ባንዱ ለብዙ ዘመናት በርካታ የባህል ሙዚቀኞችን ለሕዝብ ያደረሰ፣ በርካታ እውቅ ሙዚቀኞችን ማፍራት የቻለና ለባህል ሙዚቃ እድገት መሰረትን የጣለ መሆኑንም ጭምር ይሁኔ ይናገራል። ‹‹የኔ የሙዚቃ ሕይወት የሚጀምረው ከአካባቢ ነው። በልጅነታችን በግሽ አባይ ውስጥ የምንሰራቸው ሥራዎች የሚገርሙ ነበሩ። እርስ በእርስ የነበረን ተደጋግፎ የመስራት ልምዳችን ከፍተኛ ስለነበረ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር የማንሞካከረው ነገር አልነበረም። ከዚያ በፊት ደግሞ ትምህርት ቤት ለጓደኞቼ ስዘፍን አስተማሪዬ አይተው አንተ በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ ዘፋኝ ትሆናለህ ብለው የሰጡኝ ማበረታቻ ለዛሬው መሰረት ሆኖኛል›› በማለት በልጅነትና በባንዱ ውስጥ ያሳለፋቸውን የማይረሱ ጊዜያቶች ያስታውሳቸዋል።

ይሁኔ ከሙዚቃ ባንዱ ወጥቶ የራሱን ጉዞ በመጀመር የመጀመሪያውና የብቻው የሆነውን ‹‹ያገሬ ልጅ ባለጋሜ ትውልዷ ጎጃሜ›› የተሰኘውን አልበም በመስራት ለሕዝብ ጆሮ አበቃ። ይህ አልበሙም በመላው ኢትዮጵያ የተደመጠ ሲሆን በባህል ሙዚቃ ዘርፍ ብዙ ቅጂዎች የተሸጠ፣ የወቅቱ አንደኛና ዝነኛ አልበም ለመሆን ችሎ ነበር። በዚህ ሥራው የማህበረሰቡን ባህል አጉልቶ ያሳየበት መንገድ በትክክልም የጎጃም አምባሳደር መሆኑን ይመሰክርለታል። ስኬት የብዙ ትጋትና ጥረት ውጤት መሆኑን ያሳየበት አልበም ስለነበረ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ከመታወቅም አልፎ ለቀጣይ ስራዎቹ በር ከፋች ነበር። ዜማው ለሕዝብ ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ የይሁኔ ሕይወት አንድ በአንድ እየተለወጠ መጣ። በመጀመሪያ አልበሙ የሞራል ብርታትን ያገኘው ይሁኔ በላይ ‹‹አሎ ሎሎ›› የተሰኘ ሁለተኛው የሆነውን አልበም ለሕዝብ ጆሮ አበቃ። በመጀመሪያ ስራው የሙዚቃ መንገዱን በመጥረግ አቅንቶት ነበርና ሁለተኛ አልበሙ እንደወጣ የሕዝብ ጆሮ ለመግባት ጊዜን አልፈጀበትም። ይህን የተመለከቱ ወዳጆቹ እድለኛ መሆኑን ሲነግሩት እሱም ‹‹በእርግጥም እድለኛ ነኝ። በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ቶሎ ሕዝብ ጋር ለመድረስ ችያለሁ። ብዙ ነገሮች በሕይወቴ ውስጥ ደርሰውበኛል። ሁሉንም በእግዚአብሔር ኃይል አልፌ ለዚህ በቅቻለሁና ከምንም በላይ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ!» በማለት ይመልሳላቸዋል።

በስራዎቹ ብስለትና ክህሎቱ እያደገ የመጣው ይሁኔ በ3ኛ አልበም ሲመጣ ያለውን ኢትዮጵያዊ የሙዚቃ ለዛ በጠበቀ መልኩ ከባህል የሙዚቃ ስልት ወጣ ብሎም የአፍሪካ የሙዚቃ ስልትን በመቀላቀል መስራት ጀመረ። 3ኛው የሆነችው ‹‹ብ..ብ ከፊላው ስር›› አልበሙ የብቃቱን ደረጃና የፈጠራ ችሎታውም ማደጉን ያሳየ ነበር። ከዚህ በኋላ ‹‹ኩኩ መለኮቴ›› የተሰኘውን ሌላ አልበም አወጣ። በዚህ ወቅትም ከባለቤቱ የሺመቤት (ቱቱ) እና ከሁለቱ ወንድና ሴት ልጆቹ ጋር ኑሮው በአሜሪካን ሀገር በአሌክሳንደሪያ ቨርጂኒያ ውስጥ አድርጎ ነበረ። የነበረ በዚህ ጊዜም አንድ የማይረሳው አጋጣሚ ነበረው። ይሄውም የአሜሪካ የወቅቱ ፕሬዚዳንት ከነበሩት የቢል ክሊንተን ባለቤት ሚስ ሂላሪ ክሊንተን ጋር በመገናኘት 3ኛውን ካሴቱን በስጦታ ያበረከተበት አጋጣሚ።

ይሁኔና ቤተሰቡ ኑሯቸው በአሜሪካ ይሁን እንጂ ልጆቹ ባህላቸውን እንዳይረሱ ሁሌም እንደሚያስተምራቸው፣ እንዲሁም ወንድ ልጁን የጎጃም ሕጻናት የሚለብሱትን የባህል ካኪ ልብስ እንደሚያለብሰው የቅርብ ወዳጆቹ ይናገራሉ።

ይሁኔ በርካታ የሙዚቃ ስራዎችን መስራት የቻለ ሲሆን ናፍቀሽኛል፣ ልሳምሽ፣ ምስጋናው ደግ ነው፣ እንዳንቺ የሚያምር፣ ጉዛራ፣ ቤታችን፣ ሀይ መሎ፣ መሸለም እና ሲያምር ጨዋታው የተሰኙ አልበሞችን እና ነጠላ ዜማዎችን ከብዙ በጥቂቱ ለምሳሌነት ያህል ማንሳት ይቻላል።

ሙዚቃ ከሙዚቃነቱ ባሻገር የብዙሃን አንደበትና የውስጥ ስሜት ነው። ብዙዎች በፖለቲካና መሰል ካቴናዎች ተጠፍረው ብዕራቸው መጻፍ፣ አንደበታቸውም ማዜም በተሳነው ወቅት ይሁኔ ግን ደፈር ብሎ በትንንሽ የሙዚቃ ስንኞች ውስጥ ሀገር የሚያህል ቅኔን መቀኘት ችሏል። በኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃዎች ዐውድ በተስረቅራቂ ድምፁ ባህሉን ባከበሩ ዜማና ግጥሞች አስፍሯቸዋል። ከእነዚህ መካከልም አንዳንዶቹን ስንቃኝ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማን የተቆጣጠረው ኢህአዴግ አምስተኛ አገራዊ ምርጫ አድርጎ፣ መቶ በመቶም አሸነፍኩ ባለበት ወቅት ይሁኔ እንዲህ ሲል በውስጠ ወይራ ተቀኘ፡፡ በእርግጥ ከወቅቱ ሁኔታ አንፃር ሊሆን ይችላል ፖለቲካዊ ትርጓሜ የተሰጠው፡፡

"ላንቺ ይብላኝ እንጂ ምስጋናውን ላጣሽ፣
እኔማ ጠገቡኩሽ በህልሜ እየመጣሽ፣
ምስጋናው ደግ ነው፣ ለአልፍኝ የሚበጅ፣
እርጅና በፈረስ ደረሰበት እንጂ"

ሀገር በሰላም እጦት ውስጥ ገብታ ሳለ ባዕዳኑ በቁስሏ ላይ እንጨት ሲሰዱ ከያኒው የዛኔም ዝም አላለም።

"አትዘባበቱ ፤ቀን ጣለው ብላችሁ
ከፊታችሁ ቆሞ፤ታገኙታላችሁ" በሚል ትንቢታዊና ፍካሬያዊ ቅኔ ቅሉ ቢገባቸውም ባይገባቸውም እርሱ ግን ደህና አድርጎ ነግሯቸዋል።

ሌላው የሚኖርባትን አሜሪካ ነገረ ስራዋን ትኩር ብሎ ካጤናት በኋላ ‹‹ምስጋናው ደግ ነው›› በሚለውና ከአምስት ደቂቃዎች ብዙም በማይዘለው አሸወይና ሙዚቃው ውስጥ በመጨረሻዎቹ ስንኞች

"ይሄን ጥሩ ሙያ፤ ከቶ የት ተማርሽው፣
ስንቱን ጎበዝ ጀግና፤ወዶ ገብ አረግሽው" በማለት ጎንተል አድርጓታል።

ሀገሩ ኢትዮጵያ ጥንቱን በሀያልነትዋ ብዙ ታምራትን ሰርታ አሁን ግን በትካዜ ተፋዛ ስትቦዝን፣ ታላቅነቷን ዘንግታ መስራት ያለባትን ሳትሰራ፣ መሆን ያለባትን መሆን ሳትችል ስትቀር ይሁኔ በማራኪ ድምጹ በሚነሸጥ ዜማው እያብላላ እንዲህ አዜመላት

"እኔ እየረሳሁት ፤እሱ እያስታወሰኝ
ቸርነቱ እንዲህ ነው፤እዚህ ያደረሰኝ
መምህር መቼ ጠፋ፤ ቀሲስና አቡን
እየሳትነው እንጂ ፤ቀን ቆጠራውን"
ማን ይጎዳ ብለሽ፤ በእኔ ወድቆ መቅረት
የምድርን አይቶ ነው፤ የላይ ቤቱ ምህረት"

ጥንቱን የረታናቸው ጠላቶቻችን መልሰው ዛሬ እያባረሩን ክብራችንን እንዳይነጥቁን እያስጠነቀቀ ደግሞ

"ያደናቀፈኝ ድንጋይ፤ መልሶ ከመታኝ፣
ሳይጥል አይተወኝም፤ ሱሪ ሳያስፈታኝ" እያለ የኋላ ቀርነትና ድኅነት ምሳሌ ሆነን በንቀት መታየታችን እንደሚያንገበግበው ይገልጻል።

‹‹አንዳንድ ቀን ዘራፍ፤ ልበል እንጅ እንደ ወንድ ወተት ብቻ እኮ ነው መገፋት የሚወድ›› የሚሉት ስንኞች በአጭሩ የይሁኔን ስራዎችና ቆራጥነቱን ይገልጹታል። እሱ ላመነበትና ለሚኖርለት አላማ ወደኋላ ብሎ ነገር አያውቅምና እያቀነቀነ የሚያነቃቃ፣ እየጀገነ የሚያጀግን የጥበብ ሰው ነው።

ይሁኔ በላይ በአሁኑ ወቅት ኑሮው በአሜሪካ ሀገር ሲሆን ከባለቤቱ ጋር በመተባበር ‹‹ባውዛ›› የተሰኘ መጽሔት ያዘጋጃል። ከድምጻዊነቱ ባሻገርም የንግድ ሰው እንደሆነም ይነገርለታል። እኛም ለዚህ ከያኒ ረዥም እድሜን ከጤና ጋር ተመኘን!

# ስፖርት





# ከረጅም ርቀት ከዋክብት ጀርባ ያሉት ብርቱ ሰው

**ቦጋለ አበበ**

ከረጅም ርቀት የአትሌቲክስ ውድድር ጀግኖች መካከል ሀይሌ ገ/ስላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ ገንዘቤ ዲባባ እና ሌሎችም በእሱ ስር ሰልጥነው ነው ያለፉት። ከቅርብ ጊዜዎቹ ደግሞ ማሬ ዲባባ፣ ሰሎሞን ባረጋ፣ በሪሁ አረጋዊ፣ መቅደስ አበበ፣ ድርቤ ወልተጂ፣ ሰንበሬ ተፈሪ እና ሌሎችም የዚህ ሰው ስልጠና ተቋዳሽ በመሆን ላይ ከሚገኙት ምርጥ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው። ሰውዬው ዝነኛው የአትሌቲክስ አሰልጣኝ ሁሴን ሽቦ ነው።

የ56 ዓመቱ ጎልማሳ ወደ አትሌቲክስ አሰልጣኝነት ሙያ የገባው ከ30 ዓመታት በፊት ነው። የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን በስድስት የኦሊምፒክ እና በ25 የዓለም አገር አቋራጭ ውድድሮች ላይ በአሰልጣኝነት መርቷል። በስድስት የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ላይ ተካፍሏል። በበርካታ የቤት ውስጥ ውድድሮች ላይ አትሌቶቹን የመራ ሲሆን በ10 የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች ላይም ከፊት ሆኖ ቡድኑን መርቷል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በእሱ አሰልጣኝነት በታላላቅ ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ከ370 በላይ ሜዳሊያዎችን አግኝታለች። ይህ አስገራሚ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ዓለምን የሚያስገርም ስኬት ነው። በዚህም የተነሳ ታላላቅ የውጭ አገር መገናኛ ብዙሃን “The Medals Predator” (“ሜዳሊያ አዳኙ”) የሚል ቅፅል ስም አውጥተውለታል።

“ወደ አትሌቲክስ አሰልጣኝነት የገባሁት ገና የ25 ዓመት ወጣት ሳለሁኝ ነው። ወደ ጦር ሰራዊት ቤት መግባቴ ከአትሌቲክስ ጋር እንድተዋወቅ መንገዱን ከፍቶልኛል። እስካሁንም ድረስ የማፈቅረውን ስራ እየሰራሁ በመኖሬ በጣም ደስተኛ ነኝ። በርካታ ታላላቅ አትሌቶች በእኔ ስር ያለፉ ናቸው። ዛሬ የደረሱበትን ቦታ ስመለከት በጣም ነው የምደሰተው” ይላል ከከዋክብት አትሌቶች ጀርባ የሚገኘው ብርቱ ሰው። “ከአትሌቲክስ የተሻለ ጓደኛ የለኝም። ስራዬን በጣም ነው የምወደው። በማንኛውም ሰዓት በልምምድ ሜዳ ላይ እገኛለሁ። አትሌቶቻችን እንዴት ስኬታማ መሆን እንደሚችሉ መርዳት ያስደስተኛል። ይህ የሕይወቴ አንዱ ክፍል ነው” ሲልም ሰሞኑን ኔሽን አፍሪካ ከተባለ ድረ ገፅ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ተናግሯል።



**አሰልጣኝ ሁሴን ሽቦ**

በኦሮሚያ ክልል አርሲ የተወለደው ሁሴን ሽቦ ራሱም ሯጭ ነበር። ነገር ግን ያ ሕይወቱ በጉዳት ምክንያት ያሰበውን ያህል እንዳይጓዝ ሆኖ ከሯጭነት ዓለም ተገለለ። ክለቡ ማረሚያ ቤቶች ወደ ስልጠናው እንዲገባ ቢፈልግም እሱ ግን ፍላጎት አልነበረውም። በመሆኑም ፊቱን ወደ ሌላ ሙያ ለማዞር ሁሉ ሞክሮ ነበር። ያንን ጊዜ እንደዚህ ያስታውሰዋል።

“የሯጭነት ዘመኔ ሲያከትም በጣም ነበር የተበሳጨሁት። ምክንያቱም አሰልጣኝ የመሆን ፍላጎት አልነበረኝም። ራሴን ለስራው አላዘጋጀሁትም ነበር። እናም አዲስ አበባን ጥዬ ወደ ትውልድ ስፍራዬ አርሲ ገባሁ። ለሶስት ወራት ያህል ተምሬ መንጃ ፈቃድ አወጣሁኝና ሾፌር ለመሆን ሞከርኩኝ። ነገር ግን ጓደኞቼ የክለቤን ጥሪ እንድቀበል በመምከር ገና በ25 ዓመቴ ወደ አሰልጣኝነቱ ዓለም እንድገባ አደረጉኝ። ዛሬ ላይ ሳስበው ምክራቸውን ባልሰማ ኖሮ በሕይወቴ ሁሉ ስፀፀት እኖር እንደነበር አስባለሁ” ይላል።

አሰልጣኝ ሁሴን ሽቦ በዚህ ሁሉ ጉዞው በተለየ ሁኔታ የሚያስታውሰው የ1992 የባርሴሎና ኦሊምፒክን ነው። “ያንን ኦሊምፒክ ፈፅሞ አልረሳውም። በወቅቱ በ10 ሺህ ሜትር በማሸነፍ የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት የሆነችው ጀግኒት አትሌት ደራርቱ ቱሉ የቡድን አጋሯና አሰልጣኟ ነበርኩኝ። ነገር ግን ቡድኑ ወደ ስፍራው ሲጓዝ እኔ እንድሄድ አልተደረገም። ያ የማይረሳኝ ነው። ከዛ ውጭ ግን በስራ ዘመኔ ሁሉ መልካም ትዝታዎቼ ይገዝፋሉ” ሲል ሁኔታውን ያብራራዋል። ከድንቅ አትሌቶቻችን ጀርባ ያለው አሰልጣኝ ሁሴን ሽቦ በ2019 በአፍሪካ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የዓመቱ የአፍሪካ ኮከብ አሰልጣኝ ሆኖ መመረጡ ይታወሳል።




# ትሁቱ ታዳጊ

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ጎበዝ ልጅ ሁሌ ሳምንቱን የሚያሳልፈው በትምህርትና በጥናት ነው። እናንተም ጎበዝ ተማሪ ስለሆናችሁ ሳምንቱን ያሳለፋችሁት በትምህርት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። ጎበዝ ተማሪ የጊዜን ጥቅም በሚገባ ያውቃል ስለዚህ ያለውን ጊዜ በአግባቡ በመከፋፈል ይጠቀማል፤ ማንበብ ባለበት ሰዓት ያነባል፤ መጫወት ባለበት ሰዓት ይጫወታል፤ መማር ባለበት ሰዓት ደግሞ ይማራል። እናንተም ሰዓታችሁን እንደዚህ በስርዓት ከፋፍላችሁ እንደምትጠቀሙበት አምናለሁ።

ልጆች ዛሬ ይዤላችሁ የቀረብኩት አንደበተ-ርቱ፣ ቅን እና ቀልጣፋ የሆነውን ህፃን ኑኤል በረከትን ነው። ኑኤል የስምንት አመት ልጅ ሲሆን በቪዥን የአይነ ስውራን አፀደ ህፃናት ትምህርት ቤት የኬጂ 1 ተማሪ ነው። በዚህ አመት ከአንድ እስከ ሶስት ለመውጣት አቅዶ ትምህርቱን በትኩረት በመከታተል ላይ ይገኛል። ልጆችዬ ኑኤል ሰዎችን በእጆቹ በመንካት ማን እንደሆኑ መለየት ይችላል። የትምህርት ቤት ጓደኞቹን እና መምህራኖቹን በእጆቹ በመዳበስ ብቻ ይለያቸዋል፤ ከዚህ በተጨማሪ ግን ሰዎችን በስማቸው ይለያቸዋል። የሰዎችን ስም አንዴ ከተነገረው ሌላ ጊዜ በቀላሉ ያስታውሳል። ለምሳሌ እናንተ አንድ ቀን ኑኤልን ብታገኙትና ብትተዋወቁት ሌላ ቀን ስትገናኙ ስማችሁን አይረሳም፤ ወዲያው ያስታውሳችኋል።

የኑኤል ልዩ ችሎታ ሰው መርዳት ነው። "ሰው የምረዳው በአቅሜ ነው" የሚለው ህፃን ኑኤል ፤ አብረውት የሚማሩ ልጆች መፀዳጃ ቤት መሄድ ሲፈልጉ መፀዳጃ ቤቱ የት እንደሆነ ያሳያቸዋል፤ ወደ መማሪያ ክፍሎቻቸው መሄድ የፈለጉትንም ወደ መማሪያ ክፍሎቻቸው ያደርሳቸዋል። ልጆች ሰው መርዳት ውስጣዊ ሰላምን የሚሰጥ እጅግ በጣም ጥሩ ስራ ነው። ለተቸገረ መድረስ እና ከችግሩ እንዲወጣ መርዳት በገንዘብ የማይገዛ መንፈሳዊ እርካታን የሚሰጥ የፅድቅ ስራ ነው።

ኑኤልም ሰው በመርዳቱ የሚሰማውን ስሜት ሲገልፅ "ሰው ስረዳ ልዩ ደስታ ይሰማኛል" በማለት ነው። እናንተም ይሄንን የደስታ ስሜት ማጣጣም ከፈለጋችሁ ልክ እንደ ኑኤል ሁሉ ትንሽ ትልቅ ሳትሉ በቻላችሁት ሁሉ ሰዎችን መርዳት አለባችሁ። ህፃን ኑኤልም "ሰው እርዱ ሰው ስትረዱ እናት እና አባታችሁን ስትረዱ ደስታ ታገኛላችሁ" ለእናንተ መልእክቱን እንዳደርስ ነግሮኛል፤ እኔም ይሄው ለእናንተ አድርሻለሁ፤ እናንተ ደግሞ እንደማታሳፈሩኝ እርግጠኛ ነኝ ፤ምክሩን ትተገብራላችሁ ብዬ አምናለሁ።

ኑኤል ቤተሰቦቹ በብዙ ነገር ይደግፉታል፤ እሱም ቤተሰቦቹን የሚችለውን ስራ በመስራት ያግዛቸዋል። ሁሌ ጠዋት ጠዋት ከወላጅ አባቱ ጋር በመሆን አልጋ ያነጥፋሉ፤ ከዚያ በኋላ ቁርሱን በልቶና የመማሪያ ቁሳቁሶችን አዘጋጅቶ ሲጨርስ ወደ ትምህርት ቤት ያደርሱታል፤ ከቦታ ቦታ ሲነቀሳቀሱ የሚሄዱበት ቦታ የት እንደሆነና ስሙ ምን እንደሚባል በመንገር ቦታዎችን እንዲያውቅ ይረዱታል፤ በእግር መንገድ ሲሄዱ እጁን ይዘው እንዳይወድቅ ያግዙታል። እሱም የቤተሰቡን ምክር ስለሚሰማ ሁልጊዜም ውጤታማ ነው። ልጆች እናንተም የቤተሰቦቻችሁን ምክር ብትሰሙ እጅግ ውጤታማ ትሆናላችሁ ምክንያቱም ወላጆች ሁልጊዜ ለልጆቻቸው የሚመኙትም ሆነ የሚያደርጉት በጎ ነገር ነው።



**ህፃን ኑኤል በረከት**

ኑኤል ሲያድግ መሃንዲስ እና ቄስ መሆን ይፈልጋል። ትምህርት ሲጨርስና ትልቅ ሰው ሲሆን ቄስ በመሆን ቤተክርስቲያንን ማገልገል እና መሃንዲስ በመሆን ደግሞ ለሀገሩ የተለያዩ ውብ ህንፃዎችን መስራትና ለቤተክርስቲያንም ህንፃ መስራት ይፈልጋል። ለሀገሩ ስራ መስራት የጎደላትን መሙላት፤ የዕለት ጉርስ አጥተው የተቸገሩ እና ጎዳና የወጡ ወገኖቹን ምግብ ሰርቶ በማቅረብ መመገብ የሁልጊዜ ህልሙ ነው። የተለያዩ ተክሎችን በመትከል ኢትዮጵያን ውብ እና ሁሉም ሊያያት የሚጓጓላት ሀገር ማድረግ እና በታማኝነት ለማንም ሳያዳላ ሀገሩን ማገልገል ወደፊት አድጎ ትልቅ ልጅ ሲሆን ለሀገሩ የሚደርግላት ነገር ነው።

"ልጆች ወደፊት ኢትዮጵያን ማገዝና መርዳት አለባቸው" የሚለው ኑኤል፣ "እኔ ሀገሬ ኢትዮጵያን ማገዝ እፈልጋለሁ ልጆችም ሀገራቸውን ሊያግዙ ይገባል" በማለት ይመክራል። ውጭ ሀገር ያሉትም ለሀገራቸው ብር እንዲልኩላት እና ኢትዮጵያን በሚችሉት ሁሉ እንዲደግፏት ይፈልጋል።

ልጆች በመጨረሻም ኑኤል ለእናንተ ቆንጆ ምክር አለው፤ ልጆች ትምህርታቸውን በሚገባ በመከታተል ጎበዝ ተማሪ መሆን እንዳለባችሁ፤ እሱ ቤተሰቦቹን በስራ እንደሚያግዘው ሁሉ እናንተም ቤተሰቦቻችሁን ማገዝ እንዳለባችሁ፤ ታላላቆቻችሁና መምህራኖቻችሁ የሚሰጧችሁን ምክር መስማትና ተግባር ላይ ማዋል እንዳለባችሁ፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ሰው የመርዳት ልምዳችሁን እንድታዳብሩ ምክሩን አስተላልፏል። እኔም የኑኤልን ምክር ተግባራዊ እንድታደርጉ መልዕክቴን በማስተላለፍ ለዛሬ እዚህ ላይ ላብቃ። ሳምንት በሌላ ፅሁፍ እስክንገናኝ መልካም የትምህርት ሳምንት ይሁንላችሁ።

ልጆችዬ እንደኑኤል ጎበዝ ተማሪ መሆን አለባችሁ፤ ቤተሰባችሁን በስራ ማገዝ አለባችሁ፤ ቤተሰቦቻችሁን መስማት አለባችሁ፤ ትምህርት ቤትም ትምህርታቸውን በደንብ መከታተል አለባችሁ፤ መምህራኖቻችሁ የሚሏችሁን መስማት አለባችሁ፤ ሰው መርዳት አለባችሁ።